/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
	6304.99		-- የሹራብ ወይም የክሮሼ ሥራ ያልሆኑ፣ ከሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ፡-		
		6304.9910	--- የወባ ትንኝ መከላከያ መረቦች /አጎበር/	ኪ.ግ	ነፃ
		6304.9990	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
63.05			**ጆንያዎች እና ከረጢቶች፣ ዕቃዎችን ለመጠቅለያ የሚያገለግሉ።**		
	6305.10	6305.1000	- ከጁት ፋይበር ወይም ሌሎች በአንቀጽ 53.03 ከሚመደቡት የዕፅዋት ልጥ ፋይበሮች የተሠሩ	ኪ.ግ	20%
	6305.20	6305.2000	-- ከጥጥ የተሠሩ	ኪ.ግ	30%
			- ከሰው ሠራሽ የጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ፡-		
	6305.32	6305.3200	-- ሌሎች፣ ተጣጣፊ የመነከሰኛ በልክ ዕቃ መያዣዎች	ኪ.ግ	30%
	6305.33	6305.3300	-- ከፖሊኢቲሊን ወይም ከፖሊፕሮፒሊን ጥብጣብ ወይም ከመሳሰለው የተሠሩ	ኪ.ግ	30%
	6305.39	6305.3900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	30%
	6305.90	6305.9000	- ከሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ	ኪ.ግ	30%
63.06			**የዕቃ ማልበሻ ሽራዎች፣ መስኮት ላይ የሚዘረጉ የፀሐይና የዝናብ መከላከያ ሽራዎች እና የፀሐይ ብርሃን መከላከያ ሽራዎች፣ ድንኳኖች፣ የጀልባ፣ የትናንሽ ጀልባዎች ወይም ወደ መሬት የሚጠጉ መርከቦች ሽራዎች፣ የካምፒንግ ዕቃዎች።**		
			- የዕቃ ማልበሻ ሽራዎች፣ መስኮት ላይ የሚዘረጉ የፀሐይና የዝናብ መከላከያ ሽራዎች የፀሐይ ብርሃን መከላከያ ሽራዎች፡-		
	6306.12	6306.1200	-- ከሲንተቲክ ፋይበሮች የተሠሩ	ኪ.ግ	30%
	6306.19	6306.1900	-- ከሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ	ኪ.ግ	30%
			- ድንኳኖች፡-		
	6306.22	6306.2200	-- ከሲንተቲክ ፋይበሮች የተሠሩ	ኪ.ግ	30%
	6306.29	6306.2900	-- ከሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ	ኪ.ግ	30%
	6306.30	6306.3000	- የጀልባ ሽራ	ኪ.ግ	30%
	6306.40	6306.4000	- በአየር የሚሞሉ ፍራሾች	ኪ.ግ	30%
	6306.90	6306.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	30%
63.07			**ሌሎች የተዘጋጁ ዕቃዎች፣ የልብስ ሞዴሎች ጭምር።**		
	6307.10	6307.1000	- የወለል መወልወያ ጨርቆች፣ የሳህን መወልወያ ጨርቆች፣ የአቧራ ማራገፊያዎች እና ተመሳሳይ የማጽጃ ጨርቆች	ኪ.ግ	35%
	6307.20	6307.2000	- የመንሳፈፊያ ጃኬቶች እና ከአደጋ መከላከያ ቀበቶዎች	ኪ.ግ	35%
	6307.90	6307.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
			II. ስብስቦች		
63.08	6308.00	6308.0000	**ሸምን ጨርቅ እና ድርና ማግ የያዙ ስብስቦች፣ ከማሟያዎች ጋር ቢሆኑም ባይሆኑም፣ ለወለል ምንጣፍ፣ ለታፕስቴሪዎች፣ ለባለ ጥልፍ ጠረጴዛ ጨርቆች ወይም ለርቤት፣ ወይም ለተመሳሳይ የጨርቃ ጨርቅ ዕቃዎች መሥሪያ የሚሆኑ፣ ለችርቻሮ ሽያጭ የተዘጋጁ።**	ኪ.ግ	35%
			III. ያገለገሉ ልብሶች እና ያገለገሉ የጨርቃ ጨርቅ ዕቃዎች፣ ቁርጥራጭ ጨርቆች		
63.09	6309.00	6309.0000	**ያገለገሉ ልብሶች እና ሌሎች ያገለገሉ ዕቃዎች።**	ኪ.ግ	የተከለከለ
63.10			**ያገለገሉ ወይም አዲስ ቁርጥራጭ ጨርቆች፣ ቁርጥራጭ ሲባጎ፣ ቀጭን እና ወፍራም ገመድ እና ኬብሎች እና የሲባጎ፣ የቀጭን እና የወፍራም ገመድ ወይም የኬብል አሮጌ ዕቃዎች፣ ከጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ።**		
	6310.10	6310.1000	- በዓይነት የተለዩ	ኪ.ግ	የተከለከለ
	6310.90	6310.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	የተከለከለ

(+) 8% ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል።

ክፍል XII

ጫማዎች፣ባርኔጣዎች፣ጃንጥላዎች፣የፀሐይ መከላከያ ጥላዎች፣ የምርኩዝ ከዘራዎች፣ባለመቀመጫ ከዘራዎች፣ጅራፎች፣የፈረስኛ አለንጋዎችና የእነዚህም ክፍሎች፣ የተዘጋጁ ላባዎችና ከላባዎች የተሠሩ እቃዎች፤ አርቴፊሻል አበባዎች፤ ከሰው ፀጉር የተሠሩ ዕቃዎች

ምዕራፍ 64

ጫማዎች፣ገንባሌዎችና የመሳሰሉት፣ የእነዚሁ ዕቃዎች ክፍሎች

መግለጫ

1. ይህ ምዕራፍ የሚከተሉትንአይጨምርም፦

   ሀ/ ከልስልስ ማቴሪያሎች የሚሠሩ ከአንድ ጊዜ አገልግሎት በኋላ የሚጣሉ ሶል ያልተገጠመባቸው የአግር ወይም የጫማ ሽፋኖች/ስምሣሌ፤ ወረቀት፤ገርግ ላስቲክ/፡፡ እነዚህ ዕቃዎች ከተሠሩበት ማቴሪያል አኳያ ይመደባሉ፤

   ለ/ ከጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ ጫማዎች፤ የውጭ ሶል ያልተጣበቀባቸው፤ ያልተሰፋባቸው ወይም ከላይ ሽፋናቸው ጋር በሌላ ኳኋን ያልተገጠመባቸው /ክፍል 11/፤

   ሐ/ አሮጌ ጫማዎች በአንቀጽ 63.09 የሚመደቡ፤

   መ/ ከአስቤስቶስ የተሠሩ እቃዎች/አንቀጽ 68.12/፤

   ሠ/ የአግር በሽታ መጠገኛና ማስተካከያ ጫማዎች ወይም ሌሎች የበሽተኛ አካል መጠገኛ ዕቃዎች ወይም የእነዚህ ክፍሎች /አንቀጽ 90.21/፤ ወይም

   ረ/ አሸንጉሊት ጫማዎች ወይም መንሸራተቻ ቦት ጫማዎች የበረዶ ወይም የስስላሣ ወለል መንሸራተቻዎች በላያቸው ላይ እንደተገጠሙባቸው፤ለአግር ኪስ ጨዋታ የቅልጥም መከላከያ ፖድ ወይም ለመከላከያ የሚያገለግል ተመሣሣይ የስፖርት ትጥቅ /ምዕራፍ 95/፡፡

2. ለአንቀጽ 64.06 ሲባል፤ "ክፍሎች" የሚለው ቃል የአንጨት ወይም የብረት ችንክሮችን፤መከላከያዎች፤የጫማ ክር ማስገቢያ ቀዳዳዎችን ፤ ሜንጦዎችን ፤ ዘለበቶችን፤ ጌጦችን፤ጉንጉኖችን፤ የጫማ ማስሪያ ክሮችን፤ ማስጌጫዎችን ወይም ሌሎች መከለፊያዎችን /አግባብ ባላቸው አንቀጾች የሚመደቡትን/ ወይም ቱልፎችን ወይም ሌሎች የአንቀጽ 96.06 ዕቃዎችን አይጨምርም፡፡

3. ለዚህ ምዕራፍ ሲባል፦

   ሀ/ "ላሲቲክ" እና"ኘላስቲክስ" ማለት በዉጭ በኩል በአይን ብቻ ሊታይ በሚችል ላስቲክ ወይም ኘላስቲክ ሽምን ጨርቆችን ወይም ሌሎች ጨርቃጨርቅ ውጤቶችን ያጠቃልላል፤ለዚህ ውሣኔ ሲባል የሚከሰተው የቀለም ለውጥ ከግምት ውስጥ አይገባም፤ እና

   ለ/ የተለፋ ቆዳ የሚለው ቃል በአንቀጽ 41.07 እና ከ41.12 እስከ 41.14 ባሉት አንቀጾች የሚመደቡትን እቃዎች ይመለከታል፡፡

4. በዚህም ምዕራፍመግለጫ 3 መሠረት፦

   ሀ/ የጫማው የላይ ሽፋን ከተሠራበት ማቴሪያል በስፋት ከፍተኛውን እጅ የያዘው ሽፋኑ የተሠራበት ማቴሪያል ሆኖ ይወሰዳል፤የቁርጭምጭሚት ተለጣፊዎችን ፤ ጠርዝ መስሪያዎችን፤ ማስጌጫዎችን፤ ዘለበቶችን፤ የጫማ ክር ጫፎችን፤የጫማ ክር ማስገቢያ ቀዳዳዎችን፤ ድጋፎችን ወይም ተመሣሣይ ተለጣፊዎችን የተመሣሰሉ የሽፋኑ ክፍሎችና ማጠናከሪያዎች ከግምት ውስጥ አይገቡም ፤

   ለ/ የጫማው የውጭ ሶል የተሠራበት ማቴሪያል መሬት የሚረገጠው ሶል ከተሠራበት በሶፍት ከፍተኛውን እጅ የያዘው ሶሉ የተሠራበት ማቴሪያል ሆኖ ይወሰዳል፤ የሾሉ ኩርንችቶች፤ ጠፍጣፋ ብረቶችን፤ ምስማሮችን፤ መከላከያዎቹንና ተመሣሣይ ተለጣፊዎችን የመሣሰሉ የሶሉ ክፍሎችና ማጠናከሪያዎች ከግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

የንዑስ አንቀጽ መግለጫ

1. ለንዑስ አንቀጾች 6402.12፤6402.19፤6403.12፤6404.11 እና 6404.19 ሲባል፤ የስፖርት ጫማዎች የሚለው የሚከተሉትን ብቻ ይመለከታል፦

   ሀ/ ለስፖርት ተግባር ታስበው የተሠሩ ጫማዎች፤ የሾሉ ኩርንችቶች፤ቀጫጭን ምስማሮች፤ ማቆሚያ ነገሮች፤ ማያያገር ክሊፖች፤ ጠፍጣፋ ብረቶች ወይም እነዚህን የመሣሰሉ ነገሮች ያሏቸው ወይም እነዚህ የሚያያዙበት ቦታ የተሠራላቸው፤

   ለ/ የመንሸራተቻ ቦት ጫማዎች፤ ባለበንግ የበረዶ መንሸራተቻ የሚታሰርባቸው ቦት ጫማዎችና የአገር አቋራጭ የመንሸራተቻ ጫማዎች፤ ስኖውቦርድ ቡትስ፤ የነፃ ትግል ጫማዎች፤ የቡጢ ጨዋታ ጫማዎች እና የብስክሌተኛ ጫማዎች፡፡

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የዕቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
64.01			**የውጭው ሶሉች የላይ ሽፋኖቻቸው ክላስቲክ ወይም ከኘላስቲክ የተሠሩ ውሃ-ከል ጫማዎች ፣የላይ ሽፋኖቻቸው ከሶሉ ጋር ሳይገጣጠሙ ወጥ መስለው የተሠሩ እና በመስፋት፣ በካምሱር በማያያዝ፣ በምስማር በመምታት፣ በቢቴ በማያያዝ፣ በኘላግ በማያያዝ፣ወይም በተመሣሣይ ስራ ያልተያያዙ።**		
	6401.10	6401.1000	- ከሜታል የተሠራ የአውራ ጣት መከላከያ የተገጠመላቸው ጫማዎች	በጥንድ	35%
			- ሌሎች ጫማዎች፡-		
	6401.92	6401.9200	-- ቁርጭምጭሚት የሚሸፍኑ ነገር ግን ጉልበት የማይሸፍኑ	በጥንድ	35%
	6401.99	6401.9900	-- ሌሎች	በጥንድ	35%
64.02			**የውጭው ሶልና የላይ ሽፋኖቻቸው ክላስቲክ ወይም ከኘላስቲክ የተሠሩ ሌሎች ጫማዎች።**		
			- የስፖርት ጫማዎች ፡-		
	6402.12	6402.1200	-- ባለዘንግ የበረዶ መንሸራተቻ የሚታሰርባቸው ቦት ጫማዎች፣የአገርአቋራጭ የመንሸራተቻ ጫማዎች እና ስኖውቦርድ ቡትስ	በጥንድ	35%
	6402.19	6402.1900	-- ሌሎች	በጥንድ	35%
	6402.20	6402.2000	- የላይኛው ማሰሪያዎቻቸው ከሶሉ ጋር በኘላግ የተያያዙ ጫማዎች	በጥንድ	35%
			- ሌሎች ጫማዎች፡-		
	6402.91	6402.9100	-- ቁርጭምጭሚት የሚሸፍኑ	በጥንድ	35%
	6402.99	6402.9900	-- ሌሎች	በጥንድ	35%
64.03			**የውጭ ሶሎች ክላስቲክ፣ ከኘላስቲክ፣ ከቆዳ ወይም ከቆዳ ድብልቅ እና የላይ ሽፋኖቻቸው ከቆዳ የተሠሩ ጫማዎች።**		
			- የስፖርት ጫማዎች፡-		
	6403.12	6403.1200	-- ባለዘንግ የበረዶ መንሸራተቻ የሚታሰርባቸው ቦት ጫማዎች የአገር አቋራጭ የመንሸራተቻ ጫማዎች እና ስኖውቦርድ	በጥንድ	20%
	6403.19	6403.1900	-- ሌሎች	በጥንድ	20%
	6403.20	6403.2000	- የውጭ ሶሎች ከቆዳ የተሠሩ፣የላይ ሽፋኖቹ ከቆዳ የተሠሩ ጠፍሮች በውጭ እግር ላይ በመስቀለኛ ተላልፈው በአውራ ጣት ዙሪያ የሚጠለቁበትን ዓይነት የያዙ	በጥንድ	35%
	6403.40	6403.4000	- ሌሎች ጫማዎች፣ከሜታል የተሠራ የአውራ ጣት መከላከያ ያላቸው	በጥንድ	35%
			- ሌሎች ጫማዎች፣የውጭ ሶላቸው ቆዳ የሆነ፡-		
	6403.51	6403.5100	-- ቁርጭምጭሚት የሚሸፍኑ	በጥንድ	35%
	6403.59	6403.5900	-- ሌሎች	በጥንድ	35%
			- ሌሎች ጫማዎች፡-		
	6403.91	6403.9100	-- ቁርጭምጭሚት የሚሸፍኑ	በጥንድ	35%
	6403.99	6403.9900	-- ሌሎች	በጥንድ	35%

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የዕቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
64.04			**የውጭ ሶሎቻቸው ከላስቲክ፣ ከኘላስቲክ፣ከቆዳ ወይም ከቆዳ ድብልቅ እና የላይ ሽፋኖቻቸው ከጨርቃጨርቅ ማቴሪያል የተሠሩ ጫማዎች።**		
			- የውጭ ሶሎቻቸው ከላስቲክ ወይም ከኘላስቲክ የተሠሩ ጫማዎች፡-		
	6404.11	6404.1100	-- የስፖርት ጫማዎች፣የቴኒስ ጫማዎች፣የቅርጫት ኳስ ጫማዎች፣የጅምናዚየምጫማዎች፣ የልምምድ ጫማዎችና እነዚህን የመሳሰሉት	በጥንድ	35%
	6404.19	6404.1900	-- ሌሎች	በጥንድ	35%
	6404.20	6404.2000	- የውጭሶሎቻቸው ከቆዳ ወይም ከቆዳ ድብልቅ የተሠሩ ጫማዎች	በጥንድ	35%
64.05			**ሌሎች ጫማዎች።**		
	6405.10	6405.1000	- የላይ ሽፋኖቻቸው ከቆዳ ወይም ከቆዳ ድብልቅ የተሠሩ	በጥንድ	35%
	6405.20	6405.2000	- የላይ ሽፋኖቻቸው ከጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያል የተሠሩ	በጥንድ	35%
	6405.90	6405.9000	- ሌሎች	በጥንድ	35%
64.06			**የጫማ ክፍሎች /የላይ ሽፋኖቻቸው ጭምር፣ ከውጭ ሶሎቹ ሌላ ከሶሎቹ ጋር ቢያያዙም ባይያያዙም/፣ተነጥሎ፣ ሊነሳ የሚችል የውስጥ ሶል፣ የተረከዝ መደላደልና ተመሣሣይ ዕቃዎች፣ ገምባሌዎች፣ረጅም ገምባሌዎችና ተመሣሣይ እቃዎች፣ እና የእነዚህ ክፍሎች።**		
	6406.10	6406.1000	- የላይሽፋኖችና የእነዚህ ክፍሎች፣ ከማጠናከሪያዎች ሌላ	ኪ.ግ	20%
	6406.20	6406.2000	- የውጭ ሶሎችና ተረከዞች፣ ከላስቲክ ወይም ከኘላስቲክ የተሰሩ	ኪ.ግ	20%
	6406.90		- ሌሎች፡-		
		6406.9010	--- ከእንጨት የተሠሩ	ኪ.ግ	10%
		6406.9090	--- ከሌሎች ማቴርያሎች የተሠሩ	ኪ.ግ	20%

ምዕራፍ 65

ባርኔጣዎች፣ ቆቦችና የእነዚህም ክፍሎች

መግለጫ

1. ይህ ምዕራፍ ቀጥሎ የተመለከቱትን አይጨምርም፡-
   /ሀ/ በአንቀጽ 63.09 የሚመደቡትን አሮጌ ባርኔጣዎችና ቆቦች፣
   /ለ/ ከአስቤስቶስ የተዘጋጁ ባርኔጣዎችናቆቦች /አንቀጽ 68.12/፣ወይም
   /ሐ/ የአሸንጉሊት ባርኔጣዎች፣ሌሎች መጫወቻ ባርኔጣዎች ወይም በምዕራፍ 95 የሚመደቡ የካርኒቫል ዕቃዎች።
2. አንቀጽ 65.02 ተሰፍተው የተዘጋጁ የባርኔጣ ቅርጾችን አይጨምርም፣ ጥብጣቦችን በክብ በማሰር እየተሰሩ ከሚዘጋጁት ሌላ።

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የዕቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
65.01	6501.00	6501.0000	**የባርኔጣ ፎርሞች፣ የባርኔጣ አካሎችና ከፊልት የተሠሩ እስከ አንገት የሚጠለቁ ቆቦች፣በቅርጽ ያልተዘጋጁ እና የባርኔጣ ጠርዝ ያልተሠራላቸው፣ከፊል የተሰሩ ፕላቶና ማንሸ/ ስንጥቅ ማንሸ ጭምር/።**	ኪ.ግ	30%
65.02	6502.00	6502.0000	**የባርኔጣ ቅርጾች፣ የተጎነጎኑ ወይም ከማንኛውም ማቴሪያል ጥብጣቦች የተዘጋጁ፣በቅርጽ ያልተዘጋጁ፣ ጠርዝ ያልወጣላቸው፣ ገበርያልገባላቸው፣ እና ያልተከፈሉ።**	ኪ.ግ	30%
65.04	6504.00		**ባርኔጣዎችና ሌሎች በራስ የሚጠለቁ፣ የተጎነጎኑ ወይም ከማንኛውም ማቴሪያል ጥብጣቦች የተዘጋጁ ገበረ ያላቸው ወይም የተከፈሉ ቢሆኑም ባይሆኑም።**		
		6504.0010	--- በእጅ የተሰሩ	ኪ.ግ	35%
		6504.0090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
65.05	6505.00	6505.0000	**ባርኔጣዎችና ሌሎች በራስ የሚጠለቁ፣ የሹራብ ወይም የክሮሼ ስራ፣ወይም ከዳንቴል፣ከፊልት ወይም ከሌሎች የጨርቃጨርቅ ጣቃዎች/ንጣ ግን ጥብጣብ ያልሆኑ/የተዘጋጁ፣ ገበር ያላቸው ወይም የተከፈሉ ቢሆንም ባይሆንም፣ ከማንኛውም ማቴሪያል የተሠሩ የፀጉር መሸፈኛ መረቦች፣ገበር ያላቸው ወይም የተከፈሉ ቢሆኑም ባይሆኑም።**	ኪ.ግ	35%
65.06			**ሌሎች ባርኔጣዎችና ቆቦች፣ ገበር ያላቸው ወይም የተከፈሉ ቢሆኑም ባይሆኑም።**		
	6506.10		- የአደጋ መከላከያ ቆቦች፡-	በቁጥር	ነፃ
		6506.1010	--- የእሳት አደጋ ተከላካዮች ቆብ	በቁጥር	5%
		6506.1090	--- ሌሎች		
			- ሌሎች፡-		
	6506.91	6506.9100	-- ከላስቲክ ወይም ከኘላስቲክ የተሠሩ	ኪ.ግ	30%
	6506.99	6506.9900	-- ከሌሎች ማቴሪያሎች የተሠሩ	ኪ.ግ	30%
65.07	6507.00	6507.0000	**የባርኔጣ የውስጥ ጥብጣብ፣ገበሮች፣ ሽፋኖች፣ የባርኔጣው መሠረቶች፣የባርኔጣው ፍሬሞች፣ የባርኔጣው ጉልላቶችና በአንጭ የሚጠለቁ የባርኔጣው ማንገቻዎች።**	ኪ.ግ	30%

ምዕራፍ 66

ጀንጥላዎች፣ የፀሐይ መከላከያ ጀንጥላዎች፣ምርኩዝ ከዘራዎች ባለመቀመጫ ከዘራዎች፣ ጅራፎች፣ የፈረስኛ አለንጋዎች እናየእነዚህ ክፍሎች

መግለጫ

1. ይህ ምዕራፍ ቀጠሉ የተመለከቱትን አይጨምርም፡-

   /ሀ/ መለኪያ ያላቸው ምርኩዝ ከዘራዎችን ወይም የመሣሰሉትን /አንቀጽ 90.17/፤

   /ለ/ እንደ ጠመንጃ የሚተኩሱ ከዘራዎች፣ ባለጎራዴ ከዘራዎች፣ ጥይት የጎረሱ ምርኩዝ ከዘራዎች ወይም የመሣሰሉት/አንቀጽ 93/፤ ወይም

   /ሐ/ በምእራፍ 95 የሚመደቡ ዕቃዎች/ለምሣሌ፣አሸንጉሊት ጀንጥላዎች፣አሸንጉሊት ፀሐይ መከላከያ ጃንጥላዎች/፡፡

2. አንቀጽ 66.03 ከጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያል የተሠሩ ክፍሎችን፣መከፈፈያዎችን ወይም ማሟያዎችን፣ ወይም ከማንኛውም ማቴሪያል የተሠሩ መሸፈኛዎችን፣ መርገፎችን፣ ጠፍር መሰል ማሰሪያዎችን፣ የጃንጥላ መያዣዎችን ወይም የመሣሰሉትን አይጨምርም፡፡ እነዚህ ዕቃዎች በአንቀጽ 66.01 ወይም 66.02 ከሚመደቡት እቃዎች ጋር አብረው ቢገኙ፣ በእነዚህ እቃዎች ላይ ካልተገጠሙ በስተቀር፣ ሰብቻቸው ይመደባሉ እንጂ እንደ ክፍሎቻቸው ተቆጥረው በእነዚሁ አንቀጾች ውስጥ አይመደቡም፡፡

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
66.01			**ጃንጥላዎች እና የፀሐይ መከላከያ ጃንጥላዎች/ ከዘራነት ያላቸው ጃንጥላዎች፣የአትክልት ቦታ ጃንጥላዎች ተመሣሣይ ጃንጥላዎች ጭምር/፡፡**		
	6601.10	6601.1000	- የአትክልት ቦታ ወይም ተመሣሣይ ጃንጥላዎች	በቁጥር	35%
			- ሌሎች ፡-		
	6601.91	6601.9100	-- የቴሌስኮፕ ዘንግ ያላቸው	በቁጥር	35%
	6601.99	6601.9900	-- ሌሎች	በቁጥር	35%
66.02	6602.00		**ምርኩዝ ከዘራዎች፣ ባለመቀመጫ ከዘራዎች፣ ጅራፎች፣ የፈረስኛ አለንጋዎችና የመሣሰሉት፡፡**		
		6602.0010	--- የከበሩ ሜታሎች ወይም የተጠቀለሉ የከበሩ ሜታሎች፣ ወይም የገዘፈ ጥርሶች ወይም በሙሉ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች ያሉባቸው	በቁጥር	35%
		6602.0090	--- ሌሎች	በቁጥር	35%
66.03			**በአንቀጽ 66.01 ወይም 66.02 ለሚመደቡ እቃዎች የሚሆኑ ክፍሎች፣መከፈፈያዎችና ማሟያዎች፡፡**		
	6603.20	6603.2000	- የጃንጥላ ፍሬሞች፣ከዘንጉ ጋር የተያያዙ ፍሬሞች ጭምር	ኪ.ግ	20%
	6603.90		- ሌሎች ፡-		
		6603.9010	--- በአንቀጽ 66.01 ለሚመደቡ እቃዎች የሚሆኑ ሌሎች እቃዎች	ኪ.ግ	20%
		6603.9090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35%

ምዕራፍ 67

የተዘጋጁ ላባዎችና ለስላሣ የውስጥ ላባዎች እና ከላባዎች ወይም ከለስላሳየውስጥ ላባዎች የተሠሩእቃዎች፤ አርቴፊሻል አበባዎች፤ከሰው ፀጉር የተሠሩ እቃዎች

መግለጫ

1. ይህ ምዕራፍ ቀጥሎ የተመለከቱትን አይጨምርም፡-

   /ሀ/ ከሰው ፀጉር የተዘጋጁ ማጣሪያ ጨርቆች /አንቀጽ 59.11/፤

   /ለ/ ከዳንቴል፤ ከጥልፋጥልፍ ወይም ከሌሎች ጨርቃጨርቆች የተሠሩ የአበባ ጌጣጌጦች /ክፍል 11/፤

   /ሐ/ ጫማዎች/ምዕራፍ 64/፤

   /መ/ባርኔጣዎችና ቆቦች ወይም የፀጉር መሸፈኛ መረቦች/ምዕራፍ 65/፤

   /ሠ/ አሸንጉሊቶች፤የአስፖርት መሣሪያዎች ወይም የካርኒቫል ዕቃዎች/ምዕራፍ 95/፤ ወይም

   /ረ/ ከላባ የተሠሩ የአቧራ መጥረጊያዎች፤የፖውደር መቀቢያዎች ወይም ከፀጉር የተሠሩ ወንፊቶች/ምዕራፍ 96/

2. አንቀጽ 67.01 የሚከተሉትን አይጨምርም ፡-

   /ሀ/ ላባዎች ወይም ለስላሳ የውስጥ ላባዎች ለመሙያ ወይም ለማወፈሪያ ብቻ ሆነው የሚገኙባቸው ዕቃዎች/ለምሣሌ፤በአንቀጽ 94.04 የሚመደቡ የመኝታ ዕቃዎች/፤

   /ለ/ የልብስ እቃዎች ወይም የልብስ ክፍሎች ላባዎች ወይም ለስላሳ የውስጥ ላባዎች ለመከፈፊያ ወይም ለማወፈሪያ ብቻ እንጂ በሌላ ሁኔታ የማይገኙባቸው፤ወይም

   /ሐ/አርቲፊሻል አበባዎች ወይም ቅጠሎች ወይም የእነዚሁ ክፍሎች ወይም አንቀጽ 67.02 የሚመደቡየተሠሩ እቃዎች።

3. አንቀጽ 67.02 የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

   ሀ/ የብርጭቆ ዕቃዎች /ምዕራፍ 70/፤ ወይም

   ለ/ በቅርጽ ማውጫ፤በማስመሰል ዘዴ፤በመቅረጽ፤በማተም ወይም በሌላ የአሠራር ዘዴ የተዘጋጁ፤ ወይም በማያያዝ፤ በማጣበቅ፤ አንዱን ከሌላው ጋር በመገጣጠም ወይም እነዚህን በመሣሰሉ ዘዴዎች ሣይሆን በሌላ ዘዴ የተገጣጠሙ ክፍሎችን የያዙ፤ የሸክላ፤ የድንጋይ፤ የሚታል፤የእንጨት ወይም የሌሎች ማቴሪያሎች አርቲፊሻል አበባዎች፤ ቅጠሎች ወይም ፍሬዎች።

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
67.01	6701.00	6701.0000	**የአዕዋፍ ቆዳዎችና ሌሎች ክፍሎቻቸው ከላይ ወይም ከውስጥ ለስላሳ ላባዎቻቸው ጋር፤ ላባዎች፤ የላባ ክፍሎች፤ የውስጥ ለስላሣ ላባዎችና ከነዚህ የተሠሩ እቃዎች /በአንቀጽ 05.05 ከሚመደቡት እቃዎችና ከተሠሩ ሰፋፊ የክንፍና የጭራ ላባዎች ሌላ/።**	ኪ.ግ	30%
67.02			**አርቴፊሻል አበባዎች፤ ቅጠሎችና ፍሬዎች እና የእነዚህ ክፍሎች፤ ከአርቲፊሻል አበባዎች፤ ከቅጠሎች ወይም ከፍሬዎች የተሠሩ እቃዎች።**		
	6702.10	6702.1000	- ከኘላስቲክ የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
	6702.90		- ከሌሎች ማቴሪያሎች የተሠሩ፡-		
		6702.9010	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
		6702.9090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)

(+) 10% ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል።

አንቀጽ /1/	የኤች.ኤስ ኮድ /2/	የታሪፍ ቁጥር /3/	የእቃው አይነት /4/	የመስፈሪያው ዓይነት /5/	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ /6/
67.03	6703.00	6703.0000	የሰው ፀጉር፣ የተዘጋጀ፣ እንዲሳሳ የተደረገ፣ እንዲነጣ የተደረገ ወይም በሌላ አኳኋን የተዘጋጀ፣ ሱፍ ወይም የሌሎች እንስሳት ፀጉር ወይም ሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች፣ የውሸት ፀጉሮችን ወይም የመሣሰሉትን ለመስሪያ የተዘጋጁ።	ኪ.ግ	35% (+)
67.04			የውሸት ፀጉር፣ የውሸት ጢሞች፣ ቅንድቦችና ሽፋሎች፣ረጅም የውሸት ፀጉርና የመሳሰሉት፣ ከሰው ወይም ከእንስሳት ፀጉር ወይም ከጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ፣ በሌላ ስፍራ ያልተገለጹ ወይም ያልተመለከቱ ከሰው ፀጉር የተሠሩ እቃዎች።		
			- ከሲንተቲክ ጨርቃጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ፡-		
	6704.11	6704.1100	-- ሙሉ የውሸት ፀጉር	ኪ.ግ	35% (+)
	6704.19	6704.1900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
	6704.20	6704.2000	- ከሰው ፀጉር የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
	6704.90	6704.9000	- ከሌሎች ማቴሪያሎች የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)

(+) 40% ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል

ክፍል XIII

ከድንጋይ፣ከኘላስተር፣ ከሲሚንቶ፣ ከአስቤስቶስ፣ ከማይካ ወይም ከመሳሰሉማቴሪያሎች የተሠሩ ዕቃዎች፤ የሴራሚክ ውጤቶች ፤ ብርጭቆዎችና ከብርጪቶ የተሠሩዕቃዎች

ምዕራፍ 68

ከድንጋይ፣ ከኘላስተር፣ ከሲሚንቶ፣ ከአስቤስቶስ፣ ከማይካ ወይም ከመሳሰሉ ማቴሪያሎች የተሠሩ ዕቃዎች

መግለጫ

1. ይህ ምዕራፍ ቀጥሎ የተመለከቱትን አይጨምርም፡-

   /ሀ/ በምዕራፍ 25 የሚመደቡ ዕቃዎች፤

   /ለ/ በአንቀጽ 48.10 ወይም 48.11 የሚመደቡ የተቀቡ፣ የተነከሩ ወይም የተሸፈኑ ወረቀቶችና ካርቶኖች /ለምሣሌ በማይካ ዱቄት፣ ወይም በግራፋይት የተቀቡ ወረቀቶች፣ በቢቱሚን ወይም በአስፋልት የተነከሩ ወረቀቶች/፤

   /ሐ/ በምዕራፍ 56 ወይም 59 የሚመደቡ የተቀቡ የተነከሩ ወይም የተሸፈኑ ጨርቃ ጨርቆች /ለምሣሌ፣ በማይካ ዱቄት የተቀቡ ወይም የተሸፈኑ ጨርቃ ጨርቆች፣ በቢቱሚን ወይም በአስፋልት የተነከሩ ጨርቆች/፤

   /መ/ በምዕራፍ 71 የሚመደቡ ዕቃዎች፤

   /ሠ/ የተግባረድመስሪያዎች ወይም የእነዚህ ክፍሎች ፣ በምእራፍ 82 የሚመደቡ፤

   /ረ/ በአንቀጽ 84.42 የሚመደቡ የሊቶግራፊ ድንጋዮች ፤

   /ሰ/ የኤሌክትሪክ ኢንሱሌተሮች /አንቀጽ 85.46/ወይም በአንቀጽ 85.47 የሚመደቡ የኢንሱሌቲንግ ማቴሪያሎች ተገጣጣሚዎች፤

   /ሸ/ የጥርስ ሕክምና መሣሪያዎች /አንቀጽ 90.18/፤

   /ቀ/ በምዕራፍ 91 የሚመደቡ ዕቃዎች /ለምሣሌ፣ሰዓቶችና የሰአት ቀፎዎች/፤

   /ተ/ በምዕራፍ 94 የሚመደቡ ዕቃዎች/ለምሣሌ፣ የቤት ዕቃዎች፣ መብራቶችና የመብራት ተገጠሚዎች፣ተገጣጣሚ ቤቶች /፤

   /ቸ/ በምዕራፍ 95 የሚመደቡ ዕቃዎች / ለምሳሌ፣ አሻንጉሊቶች፣ መጫወቻዎች የስፖርት እቃዎች/፤

   /ኀ/ የምዕራፍ 96.02 ዕቃዎች በምዕራፍ 96 መግለጫ 2(ለ) ከተጠቀሱ ማቴሪያሎች የተሰሩ ከሆነ፣ ወይም የአንቀጽ 96.06 ዕቃዎች (ለምሳሌ፡- አዝራሮች)፣ የአንቀጽ 96.09 ዕቃዎች (ለምሳሌ፡- ስሌት እርሳሶች)፣ የአንቀጽ 96.10 ዕቃዎች (ለምሳሌ፡-የስዕል እርሳሶች) ወይም የአንቀጽ 96.20 ዕቃዎች (ባለ አንድ አግር፣ ባለ ሁለት አግር፣ ባለ ሦስት አግር የካሜራ ወይም የሌሎች መሳሪያዎች መደገፊያ ዘንጎች እና ተመሳሳይ ዕቃዎች)፤ ወይም

   /ነ/ በምዕራፍ 97 የሚመደቡ ዕቃዎች /ለምሣሌ፣ የስነ ጥበብ ስራዎች/።

2. በአንቀጽ " 68.02" የተሠሩ የሐውልት ወይም የሕንፃ ድንጋይ" የተባለው በአንቀጽ 25.15 ወይም 25.16 ውስጥ የተጠቀሱትን ልዩ ልዩ ዓይነትድንጋዮችን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም በዚህ ዓይነት የተሠሩትን የተፈጥሮ ድንጋዮች ሁሉ ይጨምራል።/ለምሣሌ፣ኳርትዛይት ድንጋይ፣ ባልጩት ድንጋይ፣ደሎማይት ድንጋይ ስቲታይት ድንጋይ/፤ ሆኖም ስሌትን አይጨምርም ።

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
68.01	6801.00	6801.0000	**የመንገድ ንጣፎች፣ ለፍሳሽ መውረጃ ንጣፍ የሚሆኑ ጥርብ ድንጋዮችና ለእግረኛ መንገድ ንጣፍ የሚሆኑ ድንጋዮች፣ከተፈጥሮ ድንጋይ የተሠሩ /ከስሌት በቀር/።**	ኪ.ግ	30%
68.02			**የተሠሩ የሐውልት ወይም የህንፃ ድንጋዮች/ከስሌት በቀር እና ከእነዚህም የተሠሩ እቃዎች፣በአንቀጽ 68.01 ከሚመደቡት እቃዎች ሌላ፣ የሞዛይክ ኪዩቦችና ተመሣሣዮች፣ከተፈጥሮ ድንጋይ የተሠሩ/ስሌት ጭምር /፣ ድጋፍ ያለው ቢሆንም ባይሆንም፣በእርቲፊሻል መንገድ ቀለም የተቀቡ የተፈጥሮ ድንጋይ ጠጠሮች፣ ጥራቢዎችና ዱቄቶች፣ /ስሌት ጭምር/።**		
	6802.10	6802.1000	- ታይል፣ ኪዩቦች እና ተመሣሣይ እቃዎች፣ሬክታንጉላር/ስኩዌር ጭምር/ ቢሆንም ባይሆንም፣የገጹ ከፍተኛ ስፋት የጎኑ ርዝመት ከ7 ሴ.ሜ ባነሰ ስኩዌር ውስጥ ሊታቀፍ የሚችል ፣ በእርቲፊሻል መንገድ ቀለም የተቀቡ ጠጠሮች፣ጥራቢዎችና ዱቄቶች	ኪ.ግ	35%

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
			- ሌሎች የሐውልት ወይም የሕንፃ ድንጋዮችና ከነዚህ የተሠሩ እቃዎች፣ እንዲሁም የተቆረጡ ወይም በመጋዝን የተቆረጡ፣ ልሙጥ ወይም ጠፍጣፋ ገጽ ያላቸው፡-		
	6802.21	6802.2100	-- እብነበረድ፣ትራቭርታይን እና አላባስተር	ኪ.ግ	35%
	6802.23	6802.2300	-- ግራናይት	ኪ.ግ	35%
	6802.29	6802.2900	-- ሌሎች ድንጋዮች	ኪ.ግ	35%
			- ሌሎች፡-		
	6802.91	6802.9100	-- እብነበረድ፣ ትራቭርታይን እና አላባስተር	ኪ.ግ	35%
	6802.92	6802.9200	-- ሌሎች ካለካሪያስ ድንጋዮች	ኪ.ግ	35%
	6802.93	6802.9300	-- ግራናይት	ኪ.ግ	35%
	6802.99	6802.9900	-- ሌሎች ድንጋዮች	ኪ.ግ	35%
68.03	6803.00	6803.0000	**የተሠራ ስሌትና ከስሌት ወይም እርስበርስ ተሰባስቦ ከተያያዘ ስሌት የተሠሩ እቃዎች።**	ኪ.ግ	35%
38.04			**የወፍጮ ድንጋዮች፣ መሞረጃ ድንጋዮች፣ ባለመዘውር ማሣሪያዎች እና የመሳሰሉ፣ ፍሬም የሌላቸው ለመሞረጃ፣ ለማሾያ፣ ለማለስለሻ፣ለማስተካከያ ወይም ለመቅረጫ የሚያገለግሉ፣በእጅ የሚሠራባቸው፣የማሾያ ወይም የማለስለሻ ድንጋዮች፣ እና የነዚሁ ከፍሎች፣ ከተፈጥሮ ድንጋይ እርስበርስ ተሰባስበው ከተያያዙ የተፈጥሮ ወይም አርቴፊሻል ማለስለሻዎች /አብራሲቭስ/፣ ወይም ከሴራሚክ የተሠሩ፣ የሌሎች ማቴሪያሎች ከፍሎች ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም።**		
	6804.10	6804.1000	- ለመፍጨት፣ ለመሞረድ ወይም ፐልፕነት ለመለወጥ የሚያገለግሉ የወፍጮ ድንጋዮችና መሞረጃ ድንጋዮች	ኪ.ግ	10%
			- ሌሎች የወፍጮ ድንጋዮች፣የመሞረጃ ድንጋዮች ባለመዘውር መሣሪያዎች እና የመሳሰሉ፡-	ኪ.ግ	10%
	6804.21	6804.2100	-- እርስ በርስ ተሰባስቦ ከተያያዘ ሲንተቲክ ወይም የተፈጥሮ አልማዝ የተሠሩ	ኪ.ግ	10%
	6804.22	6804.2200	-- ከሌሎች እርስ በርስ ተሰባስቦ ከተያያዙ ማለስለሻዎች/አብራሲቭስ/ ወይም ከሴራሚክስ የተሠሩ	ኪ.ግ	10%
	6804.23	6804.2300	-- ከተፈጥሮ ድንጋይ የተሠሩ	ኪ.ግ	10%
	6804.30	6804.3000	- በእጅ የሚሠራባቸው የማሾያ ወይም የማለስለሻ ድንጋዮች	ኪ.ግ	10%
68.05			**የተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ ማለስለሻ ዱቄት ወይም ሽርክት መደቡ የጨርቃጨርቅ ማቴሪያል፣ የወረቀት ካርቶን ወይም የሌሎች ማቴሪያሎች የሆነ፣በቅርጽ የተቆረጡ ወይም የተሰፉ ወይም በሌላ አኳኋን የተዘጋጁ ቢሆኑም ባይሆኑም።**		
	6805.10	6805.1000	- በተሸመነ የጨርቃጨርቅ መደብ ላይ ብቻ የተሠሩ	ኪ.ግ	10%
	6805.20	6805.2000	- በወረቀት ወይም በወረቀት ካርቶን መደብ ላይ ብቻ የተሠሩ	ኪ.ግ	10%
	6805.30	6805.3000	- በሌሎች ማቴሪያሎች መደብ ላይ የተሠሩ	ኪ.ግ	10%
68.06			**የድንጋይ ሱፍ፣ የቋጥኝ ሱፍና ተመሳሳይ የማዕድን ሱፎች፣የተቀረፈ ቬርሚኩላይት፣ የተስጠጠ ሸክላ፣ አረፋ መስል የቀለጠ ድንጋይ እና ተመሣሣይ የተስጠጡ የማዕድን ማቴሪያሎች፣ የሙቀት አጋጅ፣ የድምጽ አጋጅ ወይም ድምጽ አንጻይተላለፍ ማድረጊያ የማዕድን ማቴሪያሎች ድብልቆችና ዕቃዎች፣በአንቀጽ 68.11 ወይም 68.12 ወይም በምዕራፍ 69 ከሚመደቡት ሌላ።**		
	6806.10	6806.1000	- የድንጋይ ሱፍ፣ የቋጥኝ ሱፍ እና ተመሣሣይ የማዕድን ሱፎች/ ከእነዚህም ተወጣጥቶ የተሠሩ ድብልቆች ጭምር/፣በክምችት፣በዝርግ ወይም በጥቅል የሚገኙ	ኪ.ግ	10%
	6806.20	6806.2000	- የተቀረፈ ቬርሚኩላይት፣ የተስጠጠ ሸክላ ፣አረፋ መስል የቀለጠ ድንጋይና ተመሣሣይ የተስጠጡ የማእድን ማቴሪያሎች /ከነዚህም ተወጣጥቶ የተሠሩ ድብልቆች ጭምር/	ኪ.ግ	10%
	6806.90	6806.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	10%

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
68.07			ከአስፋልት ወይም ከተመሣሣይ ማቴሪያሎች የተሠሩ እቃዎች /ለምሣሌ፣የፔትሮሊየም በቱሚን ወይም የከሰል ቅጥራን/።		
	6807.10	6807.1000	- በጥቅል	ኪ.ግ	10%
	6807.90	6807.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	10%
68.08	6808.00	6808.0000	ፖኔሎች፣ ሳንቃዎች፣ ታይልስ፣ብሎኮችና እነዚህን የመሳሰሉ የዕፅዋት ፋይበር፣ የገለባ ወይም የእንጨት ልጣጮች፣ቁርጥራጮች፣ስብርባሪዎች፣ ፍቅፋቂዎች ወይም ሌሎች ውዳቂዎች፣ ከሲሚንቶ፣ በኘላስተር ወይም ከሌሎች የማእድን ማያያዣ ጋር እርስ በርስ ተሰባስበው የተያያዙ እቃዎች።	ኪ.ግ	35%
68.09			ከፐላስተር የተሠሩ ዕቃዎች ወይም መደባቸው ፕላስተር የሆኑ ቅንብሮች ።		
			- ሳንቃዎች፣ ዝርጉች፣ ፖኔሎች፣ ታይልስ እና ተመሳሳይ እቃዎች፣ ያልተጌጡ፦		
	6809.11	6809.1100	-- መልክ በወረቀት ወይም በወረቀት ካርቶን የተሸፈነ ወይም በእነዚሁ የተጠናከረ	ኪ.ግ	35%
	6809.19	6809.1900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
	6809.90	6809.9000	- ሌሎች እቃዎች	ኪ.ግ	35%
68.10			ከሲሚንቶ፣ ከኮንክሬት ወይም ከአርቴፊሻል ድንጋይ የተሠሩ እቃዎች፣ የተጠናከሩ ቢሆኑም ባይሆኑም ።		
			- የታይልስ፣ ለእግረኛ መንገድ ንጣፍ የሚሆኑ ጥርብ ድንጋዮች፣ ጡቦች፣ተመሣሣይእቃዎች፦		
	6810.11	6810.1100	-- ለሕንፃ ስራ የሚውሉ ብሎኮችና ጡቦች	ኪ.ግ	35%
	6810.19	6810.1900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
			- ሌሎች እቃዎች፦		
	6810.91	6810.9100	-- ለሕንፃ ወይም ለሲቪል ምህንድስና አገልግሎት የሚውሉ የተገጣጠሙ ቤቶች መስሪያ እቃዎች	ኪ.ግ	35%
	6810.99	6810.9900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
68.11			ከአስቤስቶስ ስሚንቶ፣ ከሴሉሎስ ፋይበር ሲሚንቶ ወይም እነዚህን ከመሣሰሉ የተሠሩ እቃዎች።		
	6811.40	6811.4000	- አስቤስቶስ ያላቸው	ኪ.ግ	35% (+)
			- አስቤስቶስ የሌላቸው፦		
	6811.81	6811.8100	-- ቦይ የወጣላቸው ዝርጎች	ኪ.ግ	35%
	6811.82	6811.8200	-- ሌሎች ዝርጎች፣ ፖኔሎች፣ ታይልስና ተመሣሣይ እቃዎች	ኪ.ግ	35%
	6811.89	6811.8900	-- ሌሎች እቃዎች	ኪ.ግ	35%
68.12			በፋብሪካ የተሠሩ የአስቤስቶስ ፋይበሮች፣ መደባቸው አስቤስቶስ ወይም አስቤስቶስና ማግኒዚየም ካርቦኔት የሆኑ ድብልቆች፣ ከነዚህ ድብልቆች ወይም አስቤስቶስ የተሠሩ እቃዎች /ለምሣሌ፣ ክሮች፣ ሽምን ጨርቆች፣ ልብሶች፣ በራስ የሚጠለቁ፣ ጫማዎች፣ ጋስኬቶች/፣ የተጠናከሩ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ በአንቀጽ 68.11 ወይም 68.13 ከሚመደቡት ዕቃዎች ሌላ።		
	6812.80	6812.8000	- ክሮሲዶላይት የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)

(+) 20% ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል።

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
			- ሌሎች፡-		
	6812.91	6812.9100	-- ልብሶች፣ የልብስ ማሟያዎች፣ ጫማዎችና ቆቦች	ኪ.ግ	5% (+)
	6812.92	6812.9200	-- ወረቀት፣ ወፍራምና ጠንካራ ካርቶን እና ፊልት	ኪ.ግ	35% (+)
	6812.93	6812.9300	-- የታመቀ አስቤስቶስ ፋይበር መጋጠሚያ፣ በገዘርግ ወይም በጥቅል	ኪ.ግ	35% (+)
	6812.93	6812.9900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
68.13			**የፍትጊያ መከላከያ ማቴሪያልና ከእነዚህም የተሠሩ እቃዎች /ለምሣሌ፣ ዝርጎች፣ ጥቅሎች ጥብጣቦች፣ ከፋኖች ፣ ዲስኮች፣ ዋሽሮች፣ ፖዶች/፣ ያልተገጠሙ፣ ለፍሬን ፣ ለፍሪሲዮንና ለመሣሰሉት አገልግሎት የሚውሉ ፣ መደባቸው አስቤስቶስ፣ ሌሎች የማእድን ስብስታንስ ወይም ሴሌሉስ የሆኑ፣ ከጨርቃ ጨርቅ ወይም ከሌሎች ማቴሪያሎች ጋር ተጣምረው የተሠሩ ቢሆንም ባይሆንም።**		
	6813.20	6813.2000	- አስቤስቶስ ያላቸው	ኪ.ግ	35% (+)
			- አስቤስቶስ የሌላቸው ፡-		
	6813.81	6813.8100	-- የፍሬን ሽራ እና ፖዶች	ኪ.ግ	30%
	6813.89	6813.8900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
68.14			**የተዘጋጁ ማይካ እና ከማይካ የተሠሩ እቃዎች፣ እርስ በርስ ተሰባስበው የተያያዙ ወይም እንደገና የተሠሩ ማይካዎች ጭምር፣ በወረቀት፣ በወረቀት ካርቶን፣ ወይም በሌሎች ማቴሪያሎች ድጋፍነት የተሠሩ ቢሆንም ባይሆንም።**		
	6814.10	6814.1000	- እርስ በርስ ተሰባስበው የተያያዙ ወይም እንደገና የተሠሩ የማይካ ጥፍጥፎች፣ ዝርጎችና ጥብጣቦች፣ በድጋፍ ላይየተሠሩ ቢሆኑም ባይሆኑም	ኪ.ግ	35%
	6814.90	6814.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
68.15			**ከድንጋይ ወይም ከሌሎች የማእድን ስብስታንሶች የተሠሩ እቃዎች /የካርቶን ፋይበሮችን፣ ከካርቦን ፋይበርስ እና ካፒት የተሠሩ እቃዎች ጭምር/፣ በሌላ ስፍራ ያልተመለከቱ ወይም ያልተጠቀሱ።**		
	6815.10	6815.1000	- የግራፋይት ወይም የሌሎች ካርቦኖች ኤሌክትሪክል ያልሆኑ እቃዎች	ኪ.ግ	35%
	6815.20	6815.2000	- ከፒት የተሠሩ እቃዎች	ኪ.ግ	35%
			- ሌሎች እቃዎች፡-		
	6815.91	6815.9100	-- ማግኔሳይት፣ ደሎማይት ወይም ክሮማይት ያለባቸው	ኪ.ግ	35%
	6815.99	6815.9900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35%

(+) 20% ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል።

ምዕራፍ 69

የሴራሚክ ውጤቶች

መግለጫ

1. ይህ ምዕራፍ ቅርጽ ከተሰጣቸው በኋላ በእሳት የተጠበሱትን የሴራሚክ ውጤቶች ብቻ ይመለከታል።
ከ69.04 እስከ 69.14 ያሉት አንቀጾች ከ69.01 እስከ 69.03 ባሉት አንቀጾች ከሚመደቡት ውጤቶች ውጭ ያሉትን ሌሎች ውጤቶች ይመለከታል።
2. ይህ አንቀጽ የሚከተሉትን አይጨምርም፦

/ሀ/ በአንቀጽ 28.44 የሚመደቡ ውጤቶች፤

/ለ/ በአንቀጽ 68.04 የሚመደቡ እቃዎች፤

/ሐ/ በምዕራፍ 71 የሚመደቡ ዕቃዎች /ለምሣሌ፣ በማስመሰል የተሠሩ ጌጦች/፤

/መ/ በአንቀጽ 81.13 የሚመደቡ ሰርሜትሲ፤

/ሠ/ በምዕራፍ 82 የሚመደቡ ዕቃዎች፤

/ረ/ የኤሌክትሪክ ኢንሱሌተሮች /አንቀስ 85.46/ ወይም በአንቀጽ 85.47 የሚመደቡ የኤሌክትሪክ ኢንሱሌተር ማቴሪያሎች መገጣጠሚያዎች ፤

/ሰ/ ሰው ሠራሽ ጥርሶች/አንቀጽ 90.21/፤

/ሸ/ በምዕራፍ 91 የሚመደቡ ዕቃዎች/ ለመሣሌ፤ የግድግዳና የጠረጴዛ ሰዓቶች እና የሰዓት ቀፎዎች/፤

/ቀ/ በምዕራፍ 94 የሚመደቡዕቃዎች /ለምሣሌ፤የቤት ዕቃዎች፤ መብራቶች እና የመብራቅ መገጣጠሚያዎች፤ ተገጣጣሚ ቤቶች/፤

/ተ/ በምዕራፍ 95 የሚመደቡ ዕቃዎች፤ /ለምሣሌ አሻንጉሊቶች፤ መጫወቻዎች፤የስፖርት ዕቃዎች፤

/ቸ/ በምዕራፍ 96.06 የሚመደቡ ዕቃዎች /ለምሣሌ፤ አዝራሮች/ወይም በአንቀጽ 96.14 የሚመደቡ /ለምሣሌ፤ የሲጃራ ማጨሻ ፒፓዎች/፤ ወይም

/ኀ/ በምዕራፍ 97 የሚመደቡ ዕቃዎች፤/ለምሣሌ፤ የስነ ጥበብ ሥራዎች/

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
			I. ከሲሊሺየስ ቅሪት አንኳሮች ወይም ተመሣሣይ የሲሊሺየስ አፈር የተዘጋጁ ዕቃዎች፤ እና አሳት የማይደፍራቸው እቃዎች		
69.01	6901.00	6901.0000	**ከሲሊሺየስ ቅሪት አንኳሮች /ለምሣሌ፣ ከኬስል ጉር፣ ከትራፓይላት ወይም ከዲያቶማይት /ወይም እነዚሁ ከመሣሰሉ የሲሊሺየስ አፈሮች የተዘጋጁ ጡቦች፣ ብሎኮች፣ ልባጦች እና ሌሎች የሴራሚክ እቃዎች።**	ኪ.ግ	35%
69.02			**አሳት የማይደፍራቸው ጡቦች፣ ብሎኮችና ልባጦች እና እነዚሁኑ የመሣሰሉ አሳት የማይደፍራቸው ለማንባታ የሚያገለግሉ የሴራሚክ እቃዎች፣ ከሲሊሺየስ ቅሪት አንኳሮች ወይም እነዚሁ ከመሣሰሉ ከሲሊሺየስ አፈሮች ከተሠሩ እቃዎች በቀር።**		
	6902.10	6902.1000	- በነጠላ ወይም በአንድነት፣ በክብደት ከ50% የበለጠ እንደ ማግኒዚየም አክሣይድ /Mgo/ ካልሲየም አክሣይድ/CaO / ወይም ክሮሚየም አክሣይድ /Cr2O3 / የሚገልጹትን ማግኒዚየም፡ ካልሲየም/Mg፤Ca/ ወይም ክሮሚየም /Cr/ ንጥረ ነገሮች የያዙ	ኪ.ግ	5%
	6902.20	6902.2000	- በክብደት ከ50% የበለጠ ሲሊካ /BIO2 /ወይም ከነዚህ ውጤቶች ድብልቅወይም ውሑድየተገኘ አሉሙኒየምን /Al2O3/ የያዙ	ኪ.ግ	5%
	6902.90	6902.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	5%
69.03			**ሌሎች አሳት የማይደፍራቸው የሴራሚክ እቃዎች /ለምሣሌ፣ ማንጠሪያ ድስቶች፣ ማቅለጫ ድስቶች ፣ መፍልስ፣ የማንቆርቆሪያ ጡቶች፣ ውታፎች፣ መደገፊያዎች፣ የወርቅ ማንጠሪያ ድስቶች፣ ቱቦዎች፣ ቧንቧዎች፣ ልባሶች እና ዘንጎች/፣ ከሲሊሺየስ ቅሪት አንኳሮች ወይም እነዚሁኑ ከመሣሰሉ ከሲሊሺየስ ቅሪት አንኳሮች ወይም እነዚህኑ ከመሣሰሉ ከሲሊሺየስ አፈሮች ከተሠሩ እቃዎች በቀር።**		
	6903.10	6903.1000	- በክብደት ከ50% የበለጠ ግራፋይት ወይም ሌላ ካርቦን ወይም የነዚህ ውጤቶች ድብልቅ የያዙ	ኪ.ግ	5%

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
	6903.20	6903.2000	- በክብደት ከ50% የበለጠ አሉ-ሚና /Al203/ወይም የአሉ-ሚና እና የሲሊካ /Bl02/ ድብልቆችንወይም ውህዱችን የያዙ	ኪ.ግ	5%
	6903.90	6903.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	5%
			II. ሌሎች የሲራሚክ ውጤቶች		
69.04			**ለሕንፃ መሥሪያ የሚውሉ የሲራሚክ ጡቦች፣ የወለል ንጣፎች፣ መደገፊያ ወይም መሙሊያ ልባጦች እና የመሣለሉት።**		
	6904.10	6904.1000	- የሕንፃ መስሪያ ጡቦች	1000በቁጥር	35%
	6904.90	6904.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
69.05			**የጣራ ልባጦች፣ የጭስ መውጫዎች፣ የጭስ መውጫ ጉልላቶች፣ የጭስ መውጫ ቀዳዳ መለስተኛ ልባጦች፣ የአርክቴክቸር ማስጌጫዎች እና ሌሎች ለግንባታ የሚውሉ የሴራሚክ እቃዎች።**		
	6905.10	6905.1000	- የጣራ ልባጦች	ኪ.ግ	35%
	6905.90	6905.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
69.06	6906.00	6906.0000	**ሲራሚክ ቧንቧዎች፣ ኮንዲዩትስ፣ የፈሳሽ ማውረጃ ቧንቧዎች እና የቧንቧ መገጣጠሚያዎች።**	ኪ.ግ	35%
69.07			**የሴራሚክ ጥርቦችና ንጣፎች፣የምድጃ ወይም የግድግዳ ልባጦች፣የሴራሚክ ሞዛይክ ኮቦች እና የመሳለሉት፣ የተለበዱ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ የግንባታ መጠናቀቂያ ሴራሚኮች።**		
			- የሴራሚክ ጥርቦችና ንጣፎች፣የምድጃ ወይም የግድግዳ ልባጦች በንዑስ አንቀጽ 6907.30 እና በንዑስ አንቀጽ 6907.40 ከሚመደቡት በስተቀር፦		
	6907.21	6907.2100	-- የውሃ ማስረግ ኮፊሸንቱ በክብደት ልኬት ከ0.5% ያልበለጠ	ሜትር ካሬ	35%
	6907.22	6907.2200	-- የውሃ ማስረግ ኮፊሸንቱ በክብደት ልኬት ከ0.5% የበለጠ ሆኖም ከ10% ያልበለጠ	ሜትር ካሬ	35%
	6907.23	6907.2300	-- የውሃ ማስረግ ኮፊሸንቱ በክብደት ልኬት ከ10% የበለጠ	ሜትር ካሬ	35%
	6907.30	6907.3000	- ሞዛይክ ኪዩቦች እና መሰል ዕቃዎች በንዑስ አንቀጽ6907.40 ከሚመደቡት ሌላ	ሜትር ካሬ	35%
	6907.40	6907.4000	- የግንባታ መጠናቀቂያ ሴራሚኮች	ሜትር ካሬ	35%
69.09			**ከሴራሚክ የተሠሩ ለላብራቶሪ፣ በኬሚካል ወይም ለሌሎች ቴክኒካል አገልግሎት የሚውሉ እቃዎች፣ የሴራሚክ ገንዳዎች፣ ሳፋዎች እና እነዚሁኑ የመሣለሉ ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ መያዣዎች /ሬሴፕታክልስ/፣ ማሠሮዎች ማድጋዎች እና መክተቻ የሚያገለግሉ እቃዎች።**		
			- ከሴራሚክ የተሠሩ ለላብራቶሪ፣ ለኬሚካል ወይም ለሌሎች ቴክኒካል አገልግሎቶች የሚውሉ እቃዎች፦		
	6909.11	6909.1100	-- ከፖርሲሊን ወይም ከቻይና ሽክላ የተሠራ	ኪ.ግ	5%
	6909.12	6909.1200	-- በሞህስ ስኬል ሲሰካ ጥንካሬያቸው 9 የሚሆን ወይም የበለጠ	ኪ.ግ	5%
	6909.19	6909.1900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	5%

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
	6909.90	6909.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	30%
69.10			ከሴራሚክ የተሠሩ የቆሻሻ ውሃ መውረጃዎች፣ የፊት መታጠቢያ ሳህኖች፣ የፊት መታጠቢያ ሳህን ተሸካሚዎች፣ የገላ መታጠቢያ ገንዳዎች፣ ቢዴት፣ የመጸዳጃ ሳህኖች፣ ውሃ ማጠራቀሚያና መልቀቂያ ሳህን፣ መክፈያ ሳህኖችና እነዚሁ የመሳሰሉ የመጸዳጃ እቃዎች።		
	6910.10	6910.1000	- ከፖርሲሊን ወይም ከቻይና ሸክላ የተሠሩ	በቁጥር	20%
	6910.90	6910.9000	- ሌሎች	በቁጥር	20%
69.11			- ከፖርሲሊን ወይም ከቻይና ሸክላ የተሠሩ፣የጠረጴዛ እቃዎች፣ የወጥ ቤት እቃዎች፣ ሌሎች ለቤት አገልግሎት የሚውሉ እቃዎችና የንጽህና እቃዎች።		
	6911.10	6911.1000	- የጠረጴዛ እቃዎችና የወጥ ቤት እቃዎች	ኪ.ግ	35%
	6911.90	6911.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
69.12.	6912.00		ከሴራሚክ የተሠሩ የገበታ እቃዎች፣ የወጥ ቤት እቃዎች፣ ሌሎች የቤትውስጥና የመጸዳጃ እቃዎች፣ ከፖርሲሊን ወይም ከቻይና ሸክላ ከተሠሩት ሌላ።		
		6912.0010	--- የገበታ እቃዎች እና የወጥ ቤት እቃዎች	ኪ.ግ	35%
		6912.0090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
69.13			ትናንሽ ሐውልቶችና ሌሎች ጌጠኛ የሴራሚክ እቃዎች።		
	6913.10	6913.1000	- ከፖርሲሊን ወይም ከቻይና ሸክላ የተሠሩ	ኪ.ግ	35%
	6913.90		- ሌሎች፡-		
		6913.9010	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35%
		6913.9090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
69.14			ሌሎች የሴራሚክ እቃዎች።		
	6914.10	6914.1000	- ከፖርሲሊን ወይም ከቻይና ሸክለ የተሠሩ	ኪ.ግ	35%
	6914.90		- ሌሎች፡-		
		6914.9010	--- ለውሃ ማጣሪያና ማጥሪያ የሚሆኑ ፊልትሮች	ኪ.ግ	10%
		6914.9090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35%

ምዕራፍ 70

ብርጭቆና ከብርጭቆ የተሠሩ ዕቃዎች

መግለጫ

1. ይህ ምእራፍ የሚከተሉትን አይጨምርም፡-
   /ሀ/ በአንቀጽ 32.07 የሚመደቡ ዕቃዎች/ለምሣሌ፤ በሙቀት ወደ ብርጭቆነት የሚለወጡ ኤናሜሎችና አንጸባራቂ ነገሮች፤ የብርጭቆ መስሪያ ቀላጭ ማቴሪያሎች፤በዱቄት፤በጠጠር ወይም በሽርክት መልክ የሚገኝ ሌላ ብርጭቆ/፤

   /ለ/ በምእራፍ 71 የሚመደቡ እቃዎች/ ለምሣሌ፤በማስመሰል የተሠሩ ጌጦች/፤

   /ሐ/ በአንቀጽ 85.44 የሚመደቡ ክብርሃን- አስተላላፊ ፋይበሮች የተሰሩ ኬብሎች ፤ የኤሌክትሪክ ኢንሱሌተሮች /አንቀጽ 85.46/ በአንቀጽ 85.47 የሚመደቡ የኢንሱሊቲንግ ማቴሪያል መገጣጠሚያዎች፤

   /መ/ ብርሃን አስተላላፊ ፋይበሮች፤ እንደ መነጽር የተሠሩ ማመልከቻ ነገሮች፤ ሃይፖደርሚክ ሲሪንጅ፤ ሰው ሠራሽ አይኖች፤ቴርሞሜትሮች ፤ባሮሜትሮች ወይም በምእራፍ 90 የሚመደቡ ሌሎች እቃዎች፤

   /ሠ/ መብራቶች፤ ወይም የመብራት መገጣጠሚያዎች፤ አንጸባራቂ ምልክቶች፤ አንጸባራቂ ስም ያለበቸው ሰሌዳዎች ወይም እነዚሁኑ የመሣሰሉት፤በቋሚነት የተተከሉ የብርሃን ምንጭ ያሏቸው፤ ወይም በአንቀጽ 94.05 የሚመደቡ የእነዚሁ ክፍሎች፤

   /ረ/ አሸንጉሌቶች ፤መጫዎቻዎች፤ የስፖርት እቃዎች፤የጎና ዛፍ ማስጌጫዎች ወይም ሌሎች በምእራፍ 95 የሚመደቡእቃዎች/በምእራፍ 95 ለሚመደቡ አሻንጉሊቶች ወይም ሌሎች እቃዎች ያለመነኒዚም የሚያገለግሉትን የብርጭቆ አይነቶች አይጨምሩም/፤ ወይም

   /ሰ / አገራሮች፤የተገጠሙ ቴርሙሶች፤ ሽታነት ያላቸው ወይም እነዚሁ የመሳሰሉ የሚረጩ ነገሮች ወይም በምእራፍ 96 የሚመደቡ ሌሎች እቃዎች።

2. ስለአንቀጽ 70.03፤70.04 እና 70.05 ሲባል፡-
   /ሀ/ እሙቆ እንዲቀዘቅዝ ከመደረጉ በፊት በማናቸውም ሂደት ውስጥ ያለፈ ብርጭቆእንደተሠራ" አይቆጠርም፤

   /ለ/ የገርግ መስተዋቶች በቅርጽ መቆረጥ አመዳደባቸውን አይለውጠውም፤

   /ሐ/ "የሚያሠርግ፤ የሚያንፀባርቅ ወይም የማያንፀባርቅሌየር"ማለት ብርሃን የሚያሠርግ፤ለምሣሌ የኢንፍራ-ሬድ ብርሃን፤ ወይም ብርጭቆው ሙሉ ወይም ከፊል ብርሃን አስተላላፊነቱ በተወሰነ ደረጃ እንደያዘ የማንፀባረቅ ብቃቱን የሚያሻሽል፤ወይም ብርሃን ከብርጭቆው ገፅ ላይ እንዳይንፀባረቅ የሚከላክል ፤እጅ በጣምስስ የሜታል ወይም የኬሚካል ውሑድ /ለምሣሌ ሜታል አክሣይድ /ቅብ ማለት ነው።

3. በአንቀጽ 70.06 የተጠቀሱ ውጤቶች የዕቃዎች ባሕርይ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም በዚሁ አንቀጽ እንደተመደቡ ይቆያሉ።

4. ለአንቀጽ 70.19 ሲባል፤ "የብርጭቆ ሱፍ"የተባለው፡-
   /ሀ/ በክብደት ከ60% ያላነሰ ሲሰካ /SiO2/ ያለው የማዕድን ሱፍ፤

   /ለ/ ከ60% ያነሰ ሲሰካ /SiO2/ ያለው ነገር ግን በክብደት ከ5% የበለጠ አልካሊ አክስይድ K20 ወይም Na20 ወይም በክብደት ከ2% የበለጠ ቦሪክ አክሳይድ /B2O3/ ያለው የማዕድን ሱፍ ነው።ከላይ ከተጠቀሱት ዝርዝር ሁኔታዎችጋር የማይጣጣሙ የማዕድን ሱፎች በአንቀጽ 68.06 ይመደባሉ ።

5.በዚህ ታሪፍ ውስጥ "ብርጭቆ"የተባለው የቀለጠ ኳርትዝን እና ሌሎች የቀለጡ ሲሊካን ይጨምራል።

የንዑስ አንቀጽ መግለጫ

1. ለንዑስ አንቀጽ 7013.22፤7013.33፤7013.41 እና 7013.91 ሲባል "ሌድ ክሪስታል" የተባለው በክብደት 24% አነስተኛ የእርሳስ ሞኖአክሳይድ /PbO/ ያለው ብርጭቆ ብቻ ነው።

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ል!
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
70.01	7001.00		**ከሌት፣ እና ሌሎች የብርጭቆ ውጻቂና ስብርባሪ፤ የብርጭቆ ክምችት።**		
		7001.0010	--- "የኤናሚል" ብርጭቆ ክምችት	ኪ.ግ	20%
		7001.0090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	10%

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * የገቦሩክ ኮሚሽን ቁጥር 2 * Ethiopia The Federal Democratic Republic of

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
70.02			**የተድቦለቦሉ ብርጭቆዎች /በአንቀጽ 70.18 ከሚመደቡት ማይክሮስፌሮች በቀር/፣ ዘንጉች ወይም ቱባዎች፣ ስራቸው ያላለቀላቸው።**		
	7002.10	7002.1000	- ድብልቡሎች	ኪ.ግ	10%
	7002.20	7002.2000	- ዘንጉች	ኪ.ግ	10%
			- ቱቦዎች፡-		
	7002.31	7002.3100	-- ክቀለጠ ኳርትዝ ወይም ክሌላ የቀለጠ ሲልካ የተሠሩ	ኪ.ግ	10%
	7002.32	7002.3200	-- ከ 0 ዲግሪ ሲንቲ ግሬድ እስከ 300 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ባለው የመሥቶት ክልል ከ$5x10^{-6}$ በኬልሺን ያልበለጠ የንረት ሊኒየር ኮኤፊሽንት ያላቸው ብርጭቆዎች	ኪ.ግ	10%
	7002.39	7002.3900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	10%
70.03			**ቅርጽ የወጣላቸው እና የተዳመጡ ብርጭቆዎች፣ ዝርግ ወይም ፕሮፋይል የሆኑ፣ የሚያሠርግ፣ የሚያንጸባርቅ ወይም የማያንፀባርቅ ሌየር ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ፣ ነገር ግን ከዚህ በተለየ አኳኋን ያልተሠሩ።**		
			- ሽቦ አልባ ዝርጉች፡-		
	7003.12	7003.1200	-- ሙሉ ለሙሉ የተቀለመ/አካላቸው የተቀለመ/ ብርሃን የሚከልሉ፣ የተቀቡ ወይም የሚያሠርግ፣ የሚያንፀባርቅ ወይም የማያንፀባርቅ ሌየር ያላቸው	ሜትር ካሬ	35%
	7003.19	7003.1900	-- ሌሎች	ሜትር ካሬ	35%
	7003.20	7003.2000	- ሽቦ ያላቸው ዝርጉች	ሜትር ካሬ	20%
	7003.30	7003.3000	- ፕሮፈይሎች	ሜትር ካሬ	20%
70.04			**የተሣቡና የተነፋ ብርጭቆዎች ዝርግ የሆኑ፣ የሚያሠርግ፣ የሚያንፀባርቅ ወይም የማያንፀባርቅ ሌየር ቢኖራቸውም፣ ባይኖራቸውም ነገር ግን ከዚህ በተለየ አኳኋን ያልተሠሩ።**		
	7004.20	7004.2000	- ብርጭቆዎች፣ ሙሉ ለሙሉ የተቀለሙ /አካላቸው የተቀለመ/፣ብርሃን የሚከልሉ፣ የተቀቡ ወይም የሚያሠርግ፣ የሚያንፀባርቅ ወይም የማያንፀባርቅ ሌየር ያላቸው	ሜትር ካሬ	35%
	7004.90	7004.9000	- ሌሎች ብርጭቆዎች	ሜትር ካሬ	35%
70.05			**ፍሎት ግላስ እና ላያቸው የለሰለሰ ወይም የተወለወሉ ብርጭቆዎች፣ ዝርግ የሆኑ፣ የሚያሠርግ ፣የሚያንፀባርቅ ወይም የማያንፀባርቅ ሌየር ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፣ ነገር ግንከዚህ በተለየ አኳኋን ያልተሠሩ።**		
	7005.10	7005.1000	- ሽቦ የሌለባቸው ብርጭቆዎች፣ የሚያሠርግ፣ የሚያንፀባርቅ ወይም የማያንፀባርቅ ሌየር ያላቸው	ሜትር ካሬ	35%
			- ሌሎች ሽቦ የሌለባቸው ብርጭቆዎች፡-		
	7005.21	7005.2100	-- አካላቸው በሙሉ የቀለም /የተቀቡ/፣ ብርሃን የሚከልሉ፣ ቀለም የተቀቡ ወይም ላያቸው እንዲለሰልስ ብቻ የተደረጉ	ሜትር ካሬ	35%
	7005.29	7005.2900	-- ሌሎች	ሜትር ካሬ	35%
	7005.30	7005.3000	- ሽቦ ያላቸው ብርጭቆዎች	ሜትር ካሬ	20%
70.06	7006.00	7006.0000	**በአንቀጽ 70.03፣ 70.04 ወይም 70.05 የሚመደቡ ብርጭቆዎች፣ የጎበጡ፣ ጠረዛቸው የተሠራ፣ የተቀረጹ፣ የተሰረሰሩ፣ መስተዋት ቅብ የተቀቡ ወይም በሌላ አኳኋን የተዘጋጁ፣ ነገር ግን ፍሬም የሌላቸው ወይም ከሌሎች ማቴሪያሎች ጋር ያልተገጠሙ ።**	ኪ.ግ	35%

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
70.07			**የአደጋ መከላከያ መስተዋቶች፣ የተጠናከሩ /ቴምፐርድ / ወይም የተደራረቡ መስተዋቶች ያሏቸው።**		
			- የተጠናከሩ፣ /ቴምፐርድ/ የአደጋ መከላከያ መስተዋቶች :-		
	7007.11		-- በተሽከርካሪዎች፣ በአይሮፕላኖች በህዋ መንኮራኩሮች ወይም በመርከቦች ውስጥ ለመገጠም በመጠንና በቅርጽ ተስማሚ የሆኑ፡-		
		7007.1110	--- በአይሮፕላን በህዋ በመንኮራኩሮች ወይም በንግድ መርከቦች ለመገጠም በመጠንና በቅርጽ ተስማሚ የሆኑ	ኪ.ግ	ነፃ
		7007.1190	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
	7007.19	7007.1900	-- ሌሎች	ሜትር ካሬ	35%
			- የተደራረቡ የአደጋ መከላከያ መስተዋቶች፡-		
	7007.21		-- በተሽከርካሪዎች፣ በአይሮፕላኖች ፣ በህዋ መንኮራኩሮች ወይም በመርከቦች ውስጥ ለመገጠም በመጠንና በቅርጽ ተስማሚ የሆኑ፡-		
		7007.2110	--- በአይሮፕላን፣ በህዋ መንኮራኩሮች ወይም በንግድ መርከቦች ለመገጠም በመጠንና በቅርጽ ተስማሚ የሆኑ	ኪ.ግ	ነፃ
		7007.2190	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
	7007.29	7007.2900	-- ሌሎች	ሜትር ካሬ	35%
70.08	7008.00	7008.0000	**ሙቀት የሚከላከሉ ድርብርብ መስተዋቶች።**	ኪ.ግ	20%
70.09			**የመልክ ማሣያ መስተዋቶች ፣ ፍሬም ቢኖራቸውም ባየኖራቸውም፣ በስተኋላ ያለን ነገር የሚያሣዩ መስተዋቶች ጭምር።**		
	7009.10	7009.1000	- ለተሽከርካሪዎች የሚያገለግሉ በስተኋላ ያለን ነገር የሚያሣዩ መስተዋቶች	ኪ.ግ	30%
			- ሌሎች፡-		
	7009.91	7009.9100	-- ፍሬም የሌላቸው	ኪ.ግ	35%
	7009.92	7009.9200	-- ፍሬም ያላቸው	ኪ.ግ	35%
70.10			**ደንበኛኖች፣ጠርሙሶች፣ፋሽኮዎች፣ስሮዎች፣ገንቦዎች፣ ፊላዎች፣እምፑሎች እና ሌሎች ከብርጪቆ የተሠሩ መያዣዎች፣ እቃዎችን ለመያዣ ወይም ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ፣ ማቆያ የሚሆኑ የብርጭቆ ማስሮዎች፣ የብርጭቆ ውታፎች፣ ክዳኖችና ሌሎች መክደኛዎች።**		
	7010.10	7010.1000	- አምፑሎች	ኪ.ግ	20%
	7010.20	7010.2000	- ውታፎች፣ ክዳኖች እና ሌሎች መክደኛዎች	ኪ.ግ	20%
	7010.90	7010.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
70.11			**የብርጭቆ ኤንቨሎፖች /አምፑሎችና ትዩቦች ጭምር /፣ ክፍት የሆኑ፣ እና የእነዚሁ የብርጭቆ ክፍሎች፣ መገጣጠሚያዎች የሌሏቸው፣ ለኤሌክትሮክ መብራቶች ለካቶድ ጨረር ትዩቦች ወይም እነዚህን ለመሳሰሉት የሚያገለግሉ።**		
	7011.10	7011.1000	- ለኤሌክትሪክ መብራቶች	ኪ.ግ	10%
	7011.20	7011.2000	- ለካቶድ ጨረር ቲዩቦች	ኪ.ግ	10%
	7011.90	7011.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	10%

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
70.13			**ለምግብ ቤት ለወጥ ቤት፣ ለመጸዳጃ ቤት፣ለቢሮ፣ ለቤት ውስጥ ማስጌጫ ወይም ለተመሣሣይ አገልግሎት የሚውሉ መስታወቶች /በአንቀጽ 70.10 ወይም 70.18 ከሚመደቡት ሌላ/።**		
	7013.10		- ከብርጭቆ ሲራሚክ የተሠሩ፡-		
		7013.1010	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	20%
		7013.1090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
			- ስቴምዌር የሆኑ መጠጫ ብርጭቆዎች፣ ከብርጭቆ ሴራሚክ ከተሠሩት ሌላ፡-		
	7013.22	7013.2200	-- ከሊድ ክሪስታል የተሠሩ	ኪ.ግ	20%
	7013.28	7013.2800	-- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
			- ሌሎች መጠጫ ብርጭቆዎች ከብርጭቆ ሲራሚክ ከተሠሩት ሌላ፡-		
	7013.33	7013.3300	-- ከሊድ ክሪስታል የተሠሩ	ኪ.ግ	20%
	7013.37	7013.3700	-- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
			- ለምግብ ቤት አገልግሎት የሚውሉ /ከመጠጫ ብርጭቆዎች ሌላ/ ወይም ለወጥ ቤት አገልግሎት የሚውሉ ብርጭቆ እቃዎች፣ ከብርጭቆ ሲራሚክ ከተሠሩት ሌላ፡-		
	7013.41	7013.4100	-- ከሊድ ክሪስታል የተሠሩ	ኪ.ግ	20%
	7013.42	7013.4200	-- ከ 0 ዲግሪ ሴ. እስከ 300 ዲግሪ ሴ. ባለው የመቀት ክልል ከ$5x10^{-6}$ በኬልቪ. ያልበለጠ የንረት ሊኒየር ኮኦፊሸንት ካላቸው ብርጭቆዎች የተሠሩ	ኪ.ግ	20%
	7013.49	7013.4900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
			- ሌሎች የብርጭቆ እቃዎች፡-		
	7013.91	7013.9100	-- ከሊድ ክሪስታል የተሠሩ	ኪ.ግ	20%
	7013.99	7013.9900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
70.14	7014.00		**ምልክት መስጫ የብርጭቆ እቃዎች እና ለመመልከቻ የሚያገለግሉ የብርጭቆ ኤሌመንቶች /በአንቀጽ 70.15 ከሚመደቡት ሌላ/፣ በመነጽር መልክ ያልተሠሩ።**		
		7014.0010	--- በተሽከርካሪዎች ውስጥ ለመገጠም ተስማሚ የሆኑ	ኪ.ግ	30%
		7014.0020	--- ምልክት መስጫዎች፣ ለባቡር፣ ለመንገድ ትራፊክ መቆጣጠሪ፣ ለወደብ ወይም ለአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳዎች የሚያገለግሉ	ኪ.ግ	ነፃ
		7014.0090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
70.15			**የግድግዳ፣ የጠረጴዛ ወይም የእጅ ስዓት መስታወቶች እና እነዚህ የመሣሰሉ መስታወቶች፣ የአይን በሽተኞች ለሆኑ ወይም ላልሆኑ የሚያገለግሉ መነጽሮች መሥሪያ ብርጭቆዎች፣ ቆልማማ፣ ጉባጣ ውስጠ- ከፍት የሆኑ ወይም የመሣሰሉት፣ በመነጽር መልክ ያልተሠሩ፣ ውስጥ- ከፍት የሆኑ ክብ መስታወቶችና፣ የእነዚሁ ክፋዮች፣ እንደነዚህ ያሉትን መስታወቶች በፋብሪካ ሠርቶ ለማውጣት የሚያገለግሉ።**		
	7015.10	7015.1000	- ለዓይን ሕመምተኞች መነጽር የሚያገለግሉ መስተዋቶች	ኪ.ግ	5%
	7015.90	7015.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	20%

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
70.16			**የመንገድ ንጣፎች፣ጥፍጥፎች፣ ጡቦች፣አራት ማዕዘናች፣ እና ሌሎች ከታመቀ ወይም ቅርጽ ከወጣለት ብርጭቆ የተሠሩ እቃዎች ፣ ሽቦ ያለበቸው ቢሆኑም ባይሆኑም ፣ለሕንፃ ወይም ለግንባታ አገልግሎት የሚውሉ ፤ የብርጭቆ ጠጠሮችና ትንንሽ የብርጭቆ እቃዎች ድጋፍ ያላቸው ቢሆኑም ባይሆኑም፣ ለሞዛይክና ለተመሳሳይ ማስጌጫ የሚሆኑ፣ሴድ ቅብ መብራቶችን የመሳሰሉት፣ ባለ ብዙ ጠቃጠቆ ወይ ምጉም መሰል ብርጭቆዎች፣በብሎክ በፓኔል፣ በዝርግ፣ በሼል ወይም በተመሣሣይ ቅርፆች የተዘጋጀ።**		
	7016.10	7016.1000	- ብርጭቆ ጠጠሮችና ሌሎች የብርጭቆ ትናንሽ እቃዎች፣ ድጋፍ ያላቸው ቢሆኑም ባይሆኑም፣ ለሞዛይክና ለተመሣሣይ ማጌጫ የሚሆኑ	ኪ.ግ	35%
	7016.90	7016.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
70.17			**የላብራቶር፣ የሃይጂንና የፋርማሲ የብርጭቆ እቃዎች፣ የመስፈሪያ ልክ ያላቸው ቢሆኑም ባይሆኑም።**		
	7017.10		- ቀላጭ ኳርትዝ ወይም ከሌላ ቀላጭ ሲሊካ የተሠሩ፣		
		7017.1010	--- የላብራቶር የብርጭቆ እቃዎች	ኪ.ግ	ነፃ
		7017.1090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
	7017.20		- ከ 0 ድግሪ ሴ.እስከ 300 ዲግሪ ሴ.ባለው የመቀት ክልል ከ$5x10^{-6}$ በኪልቪን ያልበለጠ የንረት ሊኒየር ኮኤፊሽንት ካላቸው ብርጭቆዎች የተሠሩ፡-		
		7017.2010	--- የላብራቶር የብርጭቆ ዕቃዎች	ኪ.ግ	5%
		7017.2090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
	7017.90		- ሌሎች፡-		
		7017.9010	--- የላብራቶሪ የብርጭቆ እቃዎች	ኪ.ግ	5%
		7017.9090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
70.18			**የብርጭቆ ጨሌዎች፣ በማስመሰል የተሠሩ እንቁዎች፣ በማስመሰል የተሠሩ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች እና ተመሣሣይ ትናንሽ የብርጭቆ እቃዎች፣ እና የእነዚሁ እቃዎች በማስመሰል ከተሠሩ የጌጣጌጥ እቃዎች ሌላ፣ የብርጭቆ ዓይኖች ከሰው - ሠራሽ የገላ ክፍሎች ሌላ፣ በመብራት ከሚሠሩ ብርጭቆዎች የተሠሩ ትናንሽ ሐውልቶችና ሌሎች ጌጣጌጦች፣ በማስመሰል ከተሠሩ ጌጣጌጥ እቃዎች ሌላ፣ ዲያሜትራቸው ከ1 ሚ.ሜ ያልበለጠ ትናንሽ ድቡልቡል ብርጭቆዎች።**		
	7018.10		- የብርጭቆ ጨሌዎች፣ በማስመሰል የተሠሩ እንቁዎች፣ በማስመሰል የተሠሩ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮችና ተመሣሣይ ትናንሽ የብርጭቆ እቃዎች ፡-		
		7018.1010	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35%
		7018.1090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35%
	7018.20	7018.2000	- ዲያሜትራቸው ከ1 ሚ.ሜ ያልበለጠ ትናንሽ ድብልቡል ብርጭቆዎች	ኪ.ግ	20%
	7018.90		- ሌሎች፡-		
		7018.9010	--- ቅርጻ ቅርጾችና በመብራት የሚሠሩ የብርጭቆ የጌጥ እቃዎች	ኪ.ግ	35%
		7018.9090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	20%

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
70.19			**የብርጭቆ ፋይበሮች/የብርጭቆ/ ሱፍ ጭምር/እና የእነዚሁ እቃዎች /ለምሣሌ፣ ድርና ማግ፣ የተሸመኑ ጨርቆች/።።**		
			- ቁልል አመልማሎ፣ ሽምልል አመልማሎ፣ ድርና ማግ እና የተቆራረጡ ክሮች፡-		
	7019.11	7019.1100	-- የተቆራረጡ ክሮች ርዝመታቸው ከ50ሚ.ሜ የማይበልጥ	ኪ.ግ	20%
	7019.12	7019.1200	-- ሽምልል አመልማሎ	ኪ.ግ	20%
	7019.19	7019.1900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
			- ስስ ጨርቆች/ቮይልስ/፣ ሽምኖች፣ ማጠናከሪያዎች፣ ፍራሾች፣ ስሊዳዎች እና ተመሣሣይ ያልተሸመኑ ውጤቶች፡-		
	7019.31	7019.3100	-- ማጠናከሪያዎች	ኪ.ግ	20%
	7019.32	7019.3200	-- ስስ ጨርቆች /ቮይልስ/	ኪ.ግ	20%
	7019.39	7019.3900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
	7019.40	7019.4000	- ከሽምልል አመልማሎ የተሸመኑ ጨርቆች	ኪ.ግ	20%
			- ሌሎች የተሸመኑ ጨርቆች፡-		
	7019.51	7019.5100	-- ወርዳቸው ከ30 ሣ.ሜ ያልበለጠ	ኪ.ግ	20%
	7019.52	7019.5200	-- ወርዳቸው ከ30 ሣ.ሜ የበለጠ ልሙጥ ሽምን፣ ክብደታቸው ከ250ግ/ሜ ስኩዌር ያነሰ የአያንዳንዱ ነጠላ ድርና ማግ ልክ ከ136 ቴክስ ከማይበልጥ ፊላሜንቶች የተሸመኑ	ኪ.ግ	20%
	7019.59	7019.5900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
	7019.90	7019.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	20%
70.20	7020.00		**ሌሎች የብርጭቆ እቃዎች።።**		
		7020.0010	--- የፔርሙስ የውስጥ ብርጭቆ	ኪ.ግ	20%
		7020.0090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	20%

ክፍል XIV

የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ ዕንቁዎች፣ የከበሩ ወይም በከፊልየከበሩ ድንጋዮች፣ የከበሩ ሜታሎች፣ የከበረ ሜታል የለበሱሜታሎች እና ከነዚህም የተሠሩ እቃዎች፣ በማስመሰል የተሠሩኔጣጌጦች፣ቅንስናሽ ገንዘብ

ምዕራፍ 71

የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ እንቁዎች፣ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች፣የከበሩ ሜታሎች፣ የከበሩ ሜታል የለበሱሜታሎች፣ እና ከነዚሁም የተሠሩ እቃዎች፣ በማስመሰል የተሠሩኔጣጌጦች፣ቅንስናሽ ገንዘብ

መግለጫ

1. በክፍል 6 *መግለጫ* 1/ሀ/ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ እና ከዚህ በታች እንደተገለጸው ካልሆነ በቀር ቁጥሮ ከተመለከቱት በሙሉ ወይም በከፊል የተሠሩ እቃዎች ሁሉ፡-

   /ሀ/ የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ እንቁዎች ወይም የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች/የተፈጥሮ፣ ሲንተቲክ ወይም እንደገና የተሠሩ/፣ ወይም

   /ለ/ የከበረ ሜታል ወይምበከበረ ሜታል የለበሰ ሜታል፣ በዚህ ምእራፍ ውስጥ ይመደባሉ፡፡

2. /ሀ/ አንቀጽ 71.13፣71.14 እና 71.15 የከበረ ሜታል ወይም የከበረ ሜታልን የለበሰ ሜታል በውስጣቸው በአነስተኛ መጠን ብቻ የሚገኝባቸውን እቃዎች አይጨምሩም፣ እነዚህም እንደ ጥቃትን ተገጣጣሚዎች ወይም አነስተኛ ማስጌጫ ሆነው የሚገኙባቸውን/ለምሣሌ፣የስም መጀመሪያ ፊደሎችን የያዙ ምልክቶች፣ ጅንፎዎችና ጠርዞች/፣ <u>እና የዚህ መግለጫ ፖራግራፍ/ለ/ እንደነዚህ ያሉትን እቃዎች አይመለከትም/*/</u>

   /ለ/ አንቀጽ 71.16 የከበረ ሜታል ወይም የከበረ ሜታልን የለበሰ ሜታል የሚገኙባቸውን እቃዎች አይጨምርም /የእቃው አነስተኛ ክፍል ሆነው ከሚገኙበት ሌላ/፡፡

3 ይህ የምዕራፍ ቁጥሮ የተመለከቱትን አይጨምርም ፡-

   /ሀ/ የሜርኩሪ ቅይጥ የሆኑ የከበሩ ሜታሎች፣ ወይም ኩሎይዳል የከበሩ ሜታሎች /አንቀጽ 28.43/፣

   /ለ/ ክጀርም የፀዱ የቀዶ ህክምና /ሰርጂካል / መስፈያ ክሮች፣ የጥርስ መሙያዎች ወይም በምእራፍ 30 የሚመደቡ ሌሎች እቃዎች፣

   /ሐ/ በምዕራፍ 32 የሚመደቡ እቃዎች /ለምሣሌ፣ለስተር/፣

   /መ/ ስፖርትድ ካታሊስትስ/ አንቀጽ 38.15/፣

   /ሠ/ በምእራፍ 42 *መግለጫ* 3/ለ/ የተጠቀሱት በአንቀጽ 42.02 ወይም 42.03 የሚመደቡ እቃዎች፣

   /ረ/ በአንቀጽ 43.03 ወይም 43.04 የሚመደቡ እቃዎች፣

   /ሰ/ የክፍል 11 እቃዎች /ጨርቃጨርቅና ከጨርቃጨርቅ የተሠሩ እቃዎች/፣

   /ሸ/ ጫማዎች፣ባርኔጣዎችና ቆቦችወይም በምእራፍ 64 ወይም 65 የሚመደቡ ሌሎች እቃዎች፣

   /ቀበ/ ጃንጥላዎች፣ ምርኩዝ ክዘራዎች ወይም በምእራፍ 66 የሚመደቡ ሌሎች ዕቃዎች፣

   /ተ/ በአንቀጽ 68.04 ወይም 68.05 ወይም በምእራፍ 82 የሚመደቡ መሞረጃዎች ወይም ማለስለሻ ብርጭቆ ወረቀት መሰል ነገሮች፣ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች የተፈጥሮ ወይም ሲንተቲክ የሆኑ /ብናኝ/ወይም ዱቄት ያለባቸው፣ በምእራፍ 82 የሚመደቡ እቃዎች የመስሪያ ክፍሎቻቸው ከከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ /የተፈጠሮ፣ሲንተቲክ ወይም እንደገና የተሠሩ /ድንጋዮች የተሠሩ፣ የክፍል 16 ማሽነሪዎች፣ የሜካኒክ መሣሪያዎች ወይም የኤሌክትሪክ እቃዎች ፣ ወይም የእነዚሁ እቃዎች ክፍሎች፣ ሆኖም እቃዎችና የእቃዎቹ ክፍሎችሙሉ በሙሉ ከከበሩ ወይም በከፊል ከከበሩ/የተፈጥሮ ፣ ሲንተቲክ ወይም እወደገና የተሠሩ/ ድንጋዮች የተሠሩ በዚሁ ምእራፍ ውስጥ ይመደባሉ፣ ካልተገጠሙ፣ ለስታይል ከሚሆኑ ከተሠሩ ግን ያልተገጠሙ ሳፊሮች/ሰማያዊ የከበረ ድንጋይ/ እና ከአልማዞች በቀር /አንቀጽ 85.22/፣

   /ቸ/ ምዕራፍ 90፣91 ወይም 92 የሚመደቡ እቃዎች /ሣይንሣዊ መሣሪያዎች፣የሣይንሣዊ የእጅ ሰዓቶች፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች/፣

   /ኀ/ የጦርመሣሪያዎች ወይም የእነዚሁ ክፍሎች/ምእራፍ 93/፣

   /ነ/ በምእራፍ 95 *መግለጫ* 2 የተገለጹ እቃዎች፣

   /ኘ/ በምዕራፍ 96 *መግለጫ* 4 መሠረት በዚያው ምእራፍ ውስጥ የሚመደቡ ዕቃዎች፣ ወይም

---

*/ በዚህ *መግለጫ* ከስሩ የተሰመረበት ክፍል አማራጭ ተደርጎ ይወሰዳል

/ሸ/ ኦርጅናል ጥርብ ቅርጾችና ሐውልቶች/አንቀጽ 97.03/ለመታሰቢያነት የተሰበሰቡ ገዘፍ ነገሮች/አንቀጽ 97.05/ ወይም ከአንድ መቶ አመት በላይአድሜ ያላቸው ጥንታዊ የቅርብ እቃዎች/አንቀጽ 97.06/ ከተፈጥሮ ወይም ከክልቸርድ ዕንቁዎች ወይም ከከበሩ ወይም በከፊል ከከበሩ ድንጋዮች ሌላ፡፡

4. /ሀ/ "የከበረ ሜታል" ማለት ብር ወርቅና ኘላስቲነም ነው፡፡

/ለ/ "ኘላቲነም" የሚለው ቃል ኘላቲነም ፤ አሪዲየም፤ አስሚየም፤ ፖላዲየም፤ ርዲየም እና ሩተኒየም ማለት ነው፡፡

/ሐ/ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች የሚለው አባባለ በምእራፍ 96 መግለጫ 2/ለ/የተመለከቱትን ማናቸውምንም ሰብስታንሶች አይጨምርም ::

5. ለዚህ ምዕራፍ ሲባል የከበረ ሜታል ያለበት ማናቸውም አሎይ /በመቀት የተደባለቀ እና ሜታሎችያሉባቸው ውሑድ ዉምር /ከሚኖራቸው ክብደት እስከ 2% የሚሆነው የአንዱ የከበረ ሜታል ከሆነእንደከበረ ሜታል አሎይ የቆጠራል፡፡ የከበረ ሜታል አሎይስ በሚከተሉት ደንቦች መሠረት ይመደባሉ፡-

/ሀ/ በክብደት 2% ወይም የበለጠ ኘላቲነም ያለበት አሎይ እንደ ኘላቲነም አሎይ ይቆጠራል፤

/ለ/ በክብደት 2% ወይም የበለጠ ወርቅ ያለበት ነገር ግንኘላቲነም የሌለበት፤ ወይም በክብደትከ2% ያላነሰ ኘላቲነም ያለበት እንደ ወርቅ አሎይ ይቆጠራል፤

/ሐ/ በክብደት 2% ወይም የበለጠ ብር ያለባቸው ሌሎች አሎይዎች እንደ ብር አሎይ ይቆጠራል፡፡

6. የቃሉ አገባብ በሌላ አኳኋን እንዲገለጽ ካላስፈለገ በቀር በዚህ ታሪፍ ውስጥ የከበረ ሜታል ወይም አንድ የተለየ የከበረ ሜታል ሲባል አባበሉ ከላይ በመግለጫ 5 ውስጥ በተመለከቱት ደንቦች መሠረት እንደከበረ ሜታል አሎይስ ወይም እንደ አንድ የተለየ ሜታልአሎይስ የሚቆጠሩትን ይጨምራል፤ ነገር ግን የከበረ ሜታል የለበሰ ሜታልን ወይም የከበረ ሜታል የተቀባ ቤዝ ሜታልን ወይም ሜታል ያልሆኑ ነገሮችን አይጨምርም፡፡

7. ከታሪፉ ውስጥ በማንኛውም ስፍራ"የከበረ ሜታልን የለበሰ ሜታል$ ማለት መሠረቱ ሜታል የሆነና በብየዳ፤ በብራዚንግ፤ በማያያዝ፤በግለት ዳምጦ በማጣበቅ ወይም በመሣሰሉው ሜካኒካዊ ዘዴ አንዱ ወይም የበለጡ ገጾች የከበረ ሜታል የለበለ ማቴሪያል ማለት ነው፡፡ የቃሉ አግባብ በሌላ አኳኋን እንዲገለጽ ካስፈለገ በቀር ይህ አባባል የከበረ ሜታል እንደማስጌጫ ሆኖ የተጨመሩበትን ቤዝ ሜታልም ይጨምራል፡፡

8. በክፍል VI መግለጫ 1/ሀ/ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 71.12 እንደተገለፁት፤ ያሉ እቃዎች በዚያው አንቀጽ ይመደባሉ እንጂ በታሪፉ ውስጥ በማናቸውም ሌላ አንቀጽ አይመደቡም ::

9. ለአንቀጽ71.13 ሲባል "የጌጣጌጥ እቃዎች" ማለት :-

/ሀ/ ማናቸውም ለግል መዋቢያ የሚውሉ ትናንሽ ጌጦች ለምሣሌ፤ቀለበቶች፤ አምባሮች፤የአንገት ሀብሎች፤የደረት ጌጦች፤የጆሮ ጉትቻዎችና ቀለበቶች፤ የሰዓት ሰንሰለቶች፤ የኪስ ሰዓት ማንጠልጠያ ሰንሰለቶች፤ ተንጠልጣይ ጌጦች፤ የከረባት ማሰሪያ መርፌ ቁልፍ፤ የሸሚዝ እጅጌ መቆለፊያዎች፤በልብስ ላይ እንደቁልፍ የሚደረጉ ጌጦች፤ የሣይማኖት ወይም ሌሎች ሜዳሊያዎች አርማዎች/፤ እና

/ለ/ በተለምዶ በኪስ፤ በእጅ ቦርሳ ወይም በሰውነት ላይ የሚደረጉ አይነት የሆኑ የግል መገልገያ አቃዎች /ለምሣሌ ሲጋራ መያዣዎች፤ሱርት መያዣዎች ፤ የአፍ ጠረን መሰወጫ እንክብሎች ወይም ኪኒን መያዣዎች፤ የፖውደር መያዣዎች፤ የሰንሰለት ቦርሳዎች፤ የጸሎት መቁጠሪያዎች/፡፡ እነዚህ አቃዎች ፤ ለምሣሌ ፤ በተፈጥሮ ወይም በአርቲፊሻል መንገድ ከተገኙክልቸርድ /ዕንቁዎች፤ ከከበሩ ወይም በከፊል ከከበሩ ድንጋዮች፤ ሲንቴቲክ ወይም እንደገና ከተሠሩ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች፤ ከኤሲ ልባስ፤ ከእንቁ እናት፤ ከአይቮሪ፤ በተፈጥሮ ወይም እንደገና ከተሠራ አምባር፤ ከጠንካራ ጥቁር ማዕድን /ጀት/ ወይም ዛኅለ ጋር የተጣመሩ ወይም በስብስብ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

10. በአንቀጽ 71.14 ሲባል "የወርቅ አንጥረኛ ወይም የብር አንጥረኛ እቃዎች" የሚለው እንደ ማስጌጫ ወይም ማስዋቢያ እቃዎች፤ የገበታ እቃዎች፤ የንጹህና መጠበቂያ እቃዎች፤ የሲጋራ ማጨሻ እቃዎች ያሉትንና ሌሉችንም የቤትውስጥ እቃዎችን የቢሮ እቃዎችን ወይም ለሣይማኖት አገልግሎት የሚውሉትን ይጨምራል፡፡

11. ለአንቀጽ 71.17 ሲባል "በማስመሰል የተሠሩ ጌጣጌጦች$ ማለት ከዚህ በላይ በመግለጫ 9 ፖራግራፍ /ሀ/ ላይ የተሰጠውን ትርጉም ይዘው የሚገኙትን የጌጣጌጥ እቃዎች/ነገር ግን በአንቀጽ 96.06 የሚመደቡትን አዝራሮች ወይ ሌሎች እቃዎችን ወይም በአንቀጽ 96.15 የሚመደቡትን ማበጠሪያ ሚዶዎችን፤ የፀጉር መያዣ ሚዶዎች ወይም እነዚህን የመሣሰሉትን ወይም የፀጉር መያዣ ሽቦዎችን ሳይጨምር/፤ የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ እንቁዎች፤ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ /የተፈጥሮ፤ ሲንተቲክ ወይም እንደገና የተሠሩ /ድንጋዮች ወይም/ እንደ ቅብ ወይም የእቃው በጣም አነስተኛ ክፍል ሆነው ከሚገኙት በቀር/ የከበሩ ሜታል ወይም የከበሩ ሜታልን የለበሱ ሜታል የሌለባቸው ማለት ነው፡፡

የንዑስ አንቀጽ መግለጫ፡፡

1. ለንዑስ አንቀጾች 7106.10፤7108.11፤ 7110.11፤ 7110.21፤እና 7110.41 ሲባል"ዱቄት" እና በዱቄት መልክ" ማለት ከጠቅላላው የዱቄት ክብደት 95% ወይም የበለጠ የሚሆነው የቀዳዳው ስፋት 0.5 ሚ.ሜ በሆነ ወንፊት ውስጥ ሊያልፍ የሚችለውን ነው፡፡

2. በዚህ ምዕራፍ መግለጫ 4/ለ/ የተወሰነው እንዳለ ሆኖ ለንዑስ አንቀጽ 7110.11 እና 7110.19 ሲባል "ፕላቲነም " የሚለው አባባል ኢሪዲየምን፤ አሉሚኒየምን፤ፓላዲየምን ሮዲየምን ወይም ሩተኒየምን አይጨምርም፡፡

3. በአንቀጽ 71.10 ሥር ባሉት ንውስ አንቀጾች ውስጥ አሎይን ለመመደብ እያንዳንዱ አሎይ፤ ከፕላቲነየም፤ ከፖላዲየም ኮሮዲየም፤ ከኢሪዲየም እና ከሩተኒየም መካከል በክብደት ከእያንዳንዱ ሜታል በልጦ ከሚገኘው ጋር ይመደባል፡፡

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
			I. የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ እንቁዎች እና የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች		
71.01			**ዕንቁዎች፣ የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ የሆኑ፣ የተሠሩ ወይም ደረጃ የወጣላቸው ቢሆንም ባይሆንም ነገር ግን በክር ያልተያያዙ፣ ያልተገጠሙ ወይም እንደ አይነታቸው ያልተከፈሉ፣ እቃዎች፣ የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ የሆኑ፣ ለትራንስፖርት ምቹነት ለጊዜው በክር የተያያዙ።**		
	7101.10	7101.1000	- የተፈጥሮ ዕንቁዎች	ኪ.ግ	35% (+)
			- ካልቸርድ ዕንቁዎች፡-		
	7101.21	7101.2100	-- ያልተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
	7101.22	7101.2200	-- የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
71.02			**አልማዞች፣ የተሠሩ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ ነገር ግን ያልተገጠሙ ወይም እንደ አይነታቸው ያልተከፈሉ።**		
	7102.10	7102.1000	- በአይነታቸው ያልተሰየ	ካራት	35% (+)
			- ለኢንዱስትሪዎች አገልግሎት የሚውሉ፡-		
	7102.21	7102.2100	-- ያልተሠሩ ወይም እንዲያው የተመገዙ፣ የተሠነጠቁ፣ ጊዜያዊ ቅርጽ የተሠጣቸው	ካራት	35% (+)
	7102.29	7102.2900	-- ሌሎች	ካራት	35% (+)
			- ለኢንዲስትሪዎች አገልግሎት የማይውሉ፡-		
	7102.31	7102.3100	-- ያልተሠሩ ወይም እንዲያው የተመገዙ፣ የተሠነጠቁ፣ ጊዜያዊ ቅርጽ የተሠጣቸው	ካራት	35% (+)
	7102.39	7102.3900	-- ሌሎች	ካራት	35% (+)
71.03			**የከበሩ ድንጋዮች/ ክአልማዞች ሌላአና በከፊል የከበሩ ድንጋዮች፣ የተሠሩ ወይም ደረጃ የወጣላቸው ቢሆኑም ባይሆኑም ነገር ግን በክር ያልተያዙ፣ ያልተገጠሙ ወይም እንደ አይነታቸው ያልተከፈሉ፣ ደረጃ ያልወጣላቸው የከበሩ ድንጋዮች/ ክአልማዞች ሌላ/ እና በከፊል የከበሩ ድንጋዮች፣ለትራንስፖርት ምቹነት ለጊዜው በክር የተያያዙ።**		
	7103.10	7103.1000	- ያልተሰሩ ወይም እንዲያው የተመገዙ፣ ወይም እንደነገሩ የተቀረጹ	ኪ.ግ	35% (+)
			- በሌላ አኳኋን የተሠሩ፡-		
	7103.91	7103.9100	-- ሩቢ፣ ሳፊር እና ኢመራልድ	ካራት	35% (+)
	7103.99	7103.9900	-- ሌሎች	ካራት	35% (+)
71.04			**ሴንተቲክ ወይም እንደገና የተሠሩ የከበሩ ወይም፣ በከፊል የከበሩ ድንጋዮች ፣ የተሠሩ ወይም ደረጃ የወጣላቸው ቢሆኑም ባይሆኑም ነገር ግን በክር ያልተያዙ፣ ያልተገጠሙ ወይም እንደ አይነታቸው ያልተከፈሉ፣ ደረጃ ያልወጣላቸው ሴንተቲክ ወይም እንደገና የተሠሩ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች ፣ ለትራንስፖርት ምቹነት ለጊዜው በክር የተያያዙ።**		
	7104.10	7104.1000	- ፒያዞ ኤሌክትሪክ ኳርትዝ	ኪ.ግ	35% (+)
	7104.20	7104.2000	- ሌሎች፣ ያልተሠሩ ወይም እንዲያው የተመገዙ ወይም እንደነገሩ የተቀረጹ	ኪ.ግ	35% (+)
	7104.90	7104.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
71.05			**የተፈጥሮ ወይም የሴንተቲክ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች ብናኝ እና ዱቄት።**		
	7105.10	7105.1000	- ከአልማዞች የተገኙ	ካራት	35% (+)
	7105.90	7105.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)

(+) 20% ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል።

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
			II. የከበረ ሜታሎችና የከበረ ሚታልን የለበሱ ሜታሎች		
71.06			ብር /ወርቅ ወይም ፕላቲነም ቅብ የሆነ ብር ጭምር/፣ በመቀጥቀጥ ቅርጽ ያልተሰጠው ወይም በከፊል የተሠራ ወይም በዱቄት መልክ የሚገኙ።		
	7106.10	7106.1000	- ዱቄት	ኪ.ግ	35% (+)
			- ሌሎች፦		
	7106.91	7106.9100	-- በመቀጥቀጥ ቅርጽ ያልተሰጣቸው	ኪ.ግ	35% (+)
	7106.92	7106.9200	-- በከፊል የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
71.07	7107.00	7107.0000	ብር የለበሱ ቤዝ ሜታሎች፣ በከፊል ከመሠራት አልፈው በሌላ አኳኋን ያልተሠሩ።	ኪ.ግ	35% (+)
71.08			ወርቅ /ፕላቲነም ቅብ የሆነ ወርቅ ጭምር/ በመቀጠቀጥ ቅርጽ ያልተሰጠው ወይም በከፊል የተሠራ ወይም በድቄት መልክ የሚገኝ ።		
			- ገንዘብ ያልሆነ፦		
	7108.11	7108.1100	-- ዱቄት	ኪ.ግ	35% (+)
	7108.12	7108.1200	-- ሌሎች በመቀጥቀጥ ቅርጽ ያልተሰጣቸው	ኪ.ግ	35% (+)
	7108.13	7108.1300	-- ሌሎች በከፊል በተሠራ መልክ	ኪ.ግ	35% (+)
	7108.20	7108.2000	- ገንዘብ የሆነ	ኪ.ግ	ነፃ
71.09	7109.00	7109.0000	ቤዝ ሜታሎች ወይም ብር፣ ወረቅ የለበሱ፣ በከፊል ከመሠራት አልፈው በሌላ አኳኋን ያልተሠሩ።	ኪ.ግ	35% (+)
71.10			ፕላቲነም፣ በመቀጥቀጥ ቅርጽ ያልተሰጠው ወይም በከፊል የተሠራ ወይም በዱቄት መልክ የሚገኝ።		
			- ፕላቲነም፦		
	7110.11	7110.1100	-- በመቀጥቀጥ ቅርጽ ያልተሰጠው ወይም በዱቄት መለክ የሚገኝ	ኪ.ግ	35% (+)
	7110.19	7110.1900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
			- ፓላዲየም፦		
	7110.21	7110.2100	-- በመቀጥቀጥ ቅርጽ ያልተሰጠ ወይም በድቄት መልክ የሚገኝ	ኪ.ግ	35% (+)
	7110.29	7110.2900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
			- ሮዲየም፦		
	7110.31	7110.3100	-- በመቀጥቀጥ ቅርጽ ያልተሰጠው ወይም በዱቄት መልክ የሚገኝ	ኪ.ግ	35% (+)
	7110.39	7110.3900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
			- ኢሪዲየም፣ ኦስሚየም እና ሩተኒየም፦		
	7110.41	7110.4100	-- በመቀጥቀጥ ቅርጽ ያልተሰጠው ወይም በዱቄት መልክ የሚገኝ	ኪ.ግ	35% (+)
	7110.49	7110.4900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
71.11	7111.00	7111.0000	ቤዝ ሜታሎች፣ ብር ወይም፣ ወርቅ፣ ፕላቲነም የለበሱ፣ በከፊል ከመሠራት አልፈው በሌላ አኳኋን ያልተሠሩ።	ኪ.ግ	35% (+)

(+) 20% ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል።

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
71.12			**የከበሩ ሜታሎች ወይም የከበሩ ሜታሎችን የለበሱ ሜታሎች ውዳቂና ቁርጥራጮች፣ የከበሩ ሜታሎች ወይም የከበሩ ሜታሎች ውሁዶች ያሉባቸው ሌሎች ወዳቂና ቁርጥራጭ በዋናነት የከበሩ ሜታሎችን ለይቶ ለማውጣት የሚውሉ።**		
	7112.30	7112.3000	- የከበሩ ሜታሎችን ወይም የከበሩ ሜታል ውህደችን የያዘ አመድ	ኪ.ግ	35% (+)
			- ሌሎች፡-		
	7112.91	7112.9100	-- ወርቅ፣ ወርቅ የለበሱ ሜታሎች ውዳቂና ቁርራጭ ጭምር ነገር ግን ሌሎች የከበረ ሜታሎች ያሉባቸውን ጥራጊዎች ሣይጨምር	ኪ.ግ	35% (+)
	7112.92	7112.9200	-- የፕላቲኒየም፣ ፕላቲኒየም የለበሱ ሜታሎች ውዳቂና ቁርጥራጭ ጭምር ነገረ ግን ሌሎች የከበሩ ሜታሎች ያሉባቸውን ጥራጊዎች ሳይጨምር	ኪ.ግ	35% (+)
	7112.99	7112.9900	-- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
			III. ጌጣጌጦች፣የወርቅ አንጥረኛና የብር አንጥረኛ እቃዎችና ሌሎች ዕቃዎች		
71.13			**የጌጣጌጥ እቃዎችና የነዚሁ ክፍሎች፣ ከከበሩ ሜታል ቅብ ወይም የከበረ ሜታልን ከለበሱ ሜታሎች የተሠሩ።**		
			- ከከበሩ ሜታሎች የተሠሩ፣ የከበሩ ሜታል ቅብ ወይም የከበረ ሜታልን የለበሱ ቢሆኑም ባይሆኑም ፡-		
	7113.11		-- ከብር የተሠሩ፣ የከበሩሜታሎች ቅብ ወይም ሌሎች የከበሩ ሜታሎችን የለበሱ ቢሆንም ባይሆኑም፡-		
		7113.1110	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
		7113.1190	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
	7113.19		-- ከሌሎች የከበሩ ሜታሎች የተሠሩ፣ የከበረ ሜታል ቅብ ወይም ሌሎች የከበሩ ሜታሎችን የለበሱ ቢሆኑም ባይሆኑም፡-		
		7113.19፲0	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
		7113.1990	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
	7113.20	7113.2000	- የከበረ ሜታልን ከለበሰ ቤዝ ሜታል የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
71.1፩			**የወርቅ አንጥረኛ ወይም የብር አንጥረኛ ዕቃዎችና የእነዚሁ ክፍሎች፣ ከከበረ ሜታል ወይም የከበረ ሜታልን ከለበ ሜታል የተሠሩ።**		
			- ከከበረ ሜታል የተሠሩ የከበረ ሜታል ቅብ ወይም የከበረ ሜታልን የለበሱ ቢሆኑም ባይሆኑም ፡-		
	7114.11		-- ከብር የተሠሩ፣ የሌሎች የከበሩ ሜታሎች ቅብ ወይም ሌሎች የከበሩ ሜታሎችን የለበሱ ቢሆኑም ባይሆኑም፡-		
		7114.1110	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
		7114.1190	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
	7114.19		-- ከሌሎች የከበሩሜታሎች የተሰሩ፣ የከበረ ሜታል ቅብ ወይም ሌሎች የከበሩ ሜታሎችን የለበሱ ቢሆኑም ባይሆኑም፡-		
		7114.1910	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
		7114.1990	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
	7114.20	7114.2000	- የከበረ ሜታልን ከለበሰ ቤዝ ሜታል የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)

(+) 20% ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል።

አንቀጽ	የኤች.ኤስ ኮድ	የታሪፍ ቁጥር	የእቃው አይነት	የመስፈሪያው ዓይነት	የጉምሩክ ቀረጥ ልክ
/1/	/2/	/3/	/4/	/5/	/6/
71.15			**ከከበረ ሜታል ወይም የከበረ ሜታልን ከለበሰ ሜታል የተሠሩ ሌሎች እቃዎች።።**		
	7115.10	7115.1000	- በሽቦ ጨርቅ ወይም ግሪል መልክ የተሰሩ የፐላቲንየም ካታሊስቶች	ኪ.ግ	5%
	7115.90		- ሌሎች፡-		
		7115.9010	--- ለላብራቶሪ ወይም ለሣይንሣዊ ተግባር ተስማሚ የሆኑ	ኪ.ግ	ነፃ
		7115.9090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
71.16			**ከተፈጥሮ ወይም ከካልቸርድ ዕንቁዎች፣ ከከበሩ ወይም በከፊል ከከበሩ /የተፈጥሮ፣ ሲንተቲክወይም እንደገና የተሠሩ/ ድንጋዮች የተሠሩ ዕቃዎች።።**		
	7116.10		- ከተፈጥሮ ወይም ከካልቸርድ እንቁዎች የተሠሩ፡-		
		7116.1010	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
		7116.1090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
	7116.20		- ከከበሩ ወይም በከፊል ከከበሩ /የተፈጥሮ፣ ሲንተቲክ ወይም እንደገና የተሠሩ/ ድንጋዮች የተሠሩ፡-		
		7116.2010	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
		7116.2090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
71.17			**በማስመሰል የተሠሩ ጌጣጌጦች።።**		
			- ከቤዝ ሜታል የተሠሩ፣ የከበረ ሜታል ቅብ ቢሆኑም ባይሆኑም፡-		
	7117.11	7117.1100	-- የሸሚዝ እጅጌ መቆለፊያዎች እና በልብስ ላይ እንደቁልፍ የሚደረጉ ጌጦች	ኪ.ግ	35 % (+)
	7117.19		-- ሌሎች፡-		
		7117.1910	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
		7117.1990	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
	7117.90		- ሌሎች ፡-		
		7117.9010	--- በእጅ የተሠሩ	ኪ.ግ	35% (+)
		7117.9090	--- ሌሎች	ኪ.ግ	35% (+)
71.18			**ቅንስናሽ ገንዘብ ።።**		
	7118.10	7118.1000	- ቅንስናሽ ገንዘብ/ከወርቅ ቅንስናሽ ገንዘብ ሌላ/ ሕጋዊ መገበያያ ገንዘብ ያልሆነ	ኪ.ግ	10%
	7118.90	7118.9000	- ሌሎች	ኪ.ግ	ነፃ

(+) 20% ኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል።።

ክፍል XV

ቤዝ ሜታልና ከቤዝ ሜታል የተሠሩ ዕቃዎች

መግለጫ

1. ይህ ክፍል ቀጥሎ የሚከተሉትን አይጨምርም:-

   /ሀ/ የተዘጋጁ የሚቀቡ ቀለሞች፤ የጽሕፈት ቀለሞች ወይም በሜታል ሽርክት ወይም ዱቄት መሠረትነት የተዘጋጁ ሌሎች ውጤቶች /አንቀጽ 32.07፤32.10፤ 32.12፤32.13 ወይም 32.15፤

   /ለ/ ፊሮ-ሰሪየም ወይምሌሎች ፓይሮፎሪክ አሎይስ/አንቀጽ 36.06/፤

   /ሐ/ በአንቀጽ 65.06 ወይም 65.07 የሚመደቡ በአራስ የሚጠለቱ ወይም የነዚሁ ክፍሎች፤

   /መ/ በአንቀጽ 66.03 የሚመደቡ የጃንጥላ ፍሬሞች ወይም ሌሎችዕቃዎች፤

   /ሠ/ በምእራፍ 71 የሚመደቡዕቃዎች፤/ለምሣሌ፤የከበሩሜታሎችአሎይ፤የከበሩ ሜታሎች የተነጠፈባቸው ቤዝሜታሎች፤ በማስመሰል የተሠሩ ጌጣጌጦች፤

   /ረ/ በክፍል XVI የሚመደቡ እቃዎች/ማሽነሪዎች፤ የሜካኒክ መሣሪያዎችና የኤሌክትሪክ እቃዎች/፤

   /ሰ/ የምድር ባቡር ወይም የትራምዌይ የተገጣጠሙ ሐዲዶች/አንቀጽ 86.08/ ወይም በክፍል XVII *የሚመደቡ ሌሎች ዕቃዎች* /ተሽከርካሪዎች፤ መርከቦችና ጀልባዎች፤ አይሮፕላኖች/፤

   /ሸ/ *ክፍል* XVIII የሚመደቡ መሣሪያዎች ወይም አፓራተስ፤ የግድግዳ፤ የጠረጴዛ ወይም የእጅ ሰዓቶች ሞላዎች ጭምር፤

   /ቀበ/የተዘጋጁ የጥይት እርሳሶች /አንቀጽ 93.06/ወይምበክፍል XIX የሚመደቡሌሎችዕቃዎች /የጦር መሣሪያዎች ጥይቶች/፤

   /ተ/ በምእራፍ 94 የሚመደቡዕቃዎች/ለምሣሌ፤ የቤት ዕቃዎች፤ የፍራሽ ድጋፎች፤ መብራቶችና የመብራት ተገጣጣሚዎች፤ ብርሃን የሚሰጡ ምልክቶች፤ ተገጣጣሚ ቤቶች/፤

   /ቸ/ በምእራፍ 95 የሚመደቡ ዕቃዎች/ለምሣሌ፤ አሻንጉሊቶች፤ መጫወቻዎች፤ የስፖርት ዕቃዎች/፤

   /ኀ/ የእጅ ወንፊቶች፤ አዝራሮች፤ ብእሮች፤ የእርሳስ መያዣዎች፤ የብዕር ጫፎች፤ ባለ አንድ እግር፤ ባለ ሁለት እግር፤ ባለ ሦስት እግር የካሜራ ወይም የሌሎች መሳሪያዎች መደገፊያ ዘንጎች እና ተመሳሳይ ዕቃዎች ወይም የምዕራፍ 96 ሌሎች ዕቃዎች (ልዩ ልዩ በፋብሪካ የተመረቱ ዕቃዎች) ፤ ወይም

   /ኀ/ በምእራፍ 97 የሚመደቡ ዕቃዎች /ለምሣሌ፤የስነ ጥበብ ስራዎች/።

2. በዚህ ታሪፍ ውስጥ #ለጠቅላላ አገልግሎት የሚውሉ የዕቃ ክፍሎች$ የሚለው አገላለጽ የሚከተሉትን ይመለከታል፡-

   /ሀ/ በአንቀጽ 73.07፤73.12፤73.15፤73.17 ወይም 73.18 የሚመደቡ ዕቃዎችና ከሌሎች ቤዝ ሜታሎች የተሠሩ ተመሣሣይ ዕቃዎች፤

   /ለ/ ከቤዝ ሜታል የተሠሩ ሞላዎችና የሞላ ቅጠሎች፤ ከግድግዳ፤ ከጠረጴዛ ወይም ከእጅ ሰዓቶች ሞላዎች ሌላ /አንቀጽ 91.14፤ እና

   /ሐ/ በአንቀጽ 83.01፤83.02፤83.10 የሚመደቡ ዕቃዎች እና በአንቀጽ 83.06 የሚመደቡ ከቤዝ ሜታል የተሠሩ ፍሬሞችና መስታወቶች።

   ከምዕራፍ 73 እስከ 76 እና ከምእራፍ 78 እስከ 82/ ነገር ግን በአንቀጽ 73.15 የሚመደቡትን ሳይጨምር /የዕቃ ክፍሎች ተብሎ የተጠቀሰው ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ለጠቅላላ አገልግሎት የሚውሉ የዕቃ ክፍሎች ለሚለው የተሰጡትን ውሣኔዎች አይጨምርም።

   ከዚህ በላይ በተገለጸው *ፓራግራፍ* መነሻነትና በምእራፍ 83 መግለጫ 1 መሠረት የምዕራፍ 82 ወይም 83 ዕቃዎች ከምዕራፍ 72 እስከ 76 እና ከ78 እስከ 81 ባሉት ምዕራፎች አይመደቡም።

3. በታሪፍ ውስጥ በማንኛውም ስፍራ"ቤዝ ሜታልስ"ማለት ብረትና የአረብ ብረት፤ መዳብ፤ ኒኬል፤አሉሚኒየም፤ ሊድ ዚንክ፤ ቆርቆሮ፤ተንግስተን ወልፍራም/፤ ሞሊብዲነም፤ ማግኒዚየም፤ ኮባልት፤ቢስሙዝ፤ ካድሚየም፤ ቲታኒየም፤ ዘፍኮኒየም፤ አንቲሞኒ፤ ዘፍኮኒየም፤ አንቲሞኒ ማንጋኒዝ፤ ቤሪሊየም፤ ኾሮማኒየም፤ ቫናዲየም፤ጋሊየም፤ሃፍኒየም፤አንዲየም /ክሎምሊየም/፤ሬኒየም እና ናታሊየም ማለት ነው።

4. በታሪፍ ውስጥ በማንኛውም ስፍራ"ሴርሜትስ" ማለት እጅግ በጣም ጥቃቅን በዓይን የማይታይ የተለያዩ የማታሊክ ኮምፓኒንት፤ እና የሴራሚክ ኮምፓኒንት ያላቸው ውጤቶች ማለት ነው።"ሰርሜትስ" የሚለው ቃል ሲንተርድ ሜታል ካርባይዱስን/ ከሜታል ጋር በግለት የተጣመሩ ሜታል ካርባይዱስ/ ይጨምራል።

5. የአሎይስ አመዳደብ/ በምዕራፍ 72 እና 74 እንደተገለፀው ከፊሮ አሎይስና ከማስተር አሎይስ ሌላ፡-

   /ሀ/ የቤዝ ሜታል አሎይ የአንድ አይነት ሜታል አሎይ ተብሎ ሊመደብ የሚችለው የሜታል በአሎይ ውስጥ ካሉት ሌሎች ሜታሎች ሁሉ በክብደት በልጦ ሲገኝ ነው፤

   /ለ/ በዚህ ክፍል የሚመደቡትን ቤዝ ሜታሎችና በዚህ ክፍል የማይመደቡትን ንጥረ ነገሮች አጣምሮ የያዘ አሎይ የቤዝ ሜታሎቹ ጠቅላላ ክብደት ከነዚህ በውስጡ ከተያዙ ሌሎች ንጥረ ነገሮች ጠቅላላ ክብደት *ጋር* እኩል ከሆነ ወይም ከበለጠ የዚህ ክፍል ቤዝ ሜታሎች አሎይ እንደሆነ ተቀጥሮ ይመደባል፤

   /ሐ/ በዚህ ክፍል ውስጥ "አሎይስ" የሚለው ቃል በመቀት የተያያዙ የሜታል ዱቄቶች ድብልቆችን፤ በማትለጥ እንዲቀላቀሉ የተደረጉትን የተለያዩ ነገሮች ድብልቆችን /ከሰረሜትስ ሌላ/ እና ሜታሎችን እርስ በርስ በማዋሐድ የተገኙትን ይጨምራል።

6. የቃሉ አግባብ በሌላ አኒኋን እንዲገለጽ ካላስፈለገ በቀር፤ በዚህ ታሪፍ ውስጥ ለቤዝ ሜታል የተሰጠው አገላለጽ ከላይ በመግለጫ 3 በተመለከተው መሠረት፤ የዚህ ሜታል አሎይስ እንደሆኑ ተቀጥረው የሚመደቡትን አሎይስ ይጨምራል።

7. ከልዩ ልዩ ማቴሪያሎች የተሠሩ ዕቃዎች አመዳደብ፡-
አንቀጾች በሌላ አኳኋን እንዲገለጹ ካልተፈለገ በቀር፤ ሁለት ወይም የበለጡ ቢዝ ሜታሎች የሚገኙባቸው የቤዝ ሜታል ዕቃዎች /በመግለማጫዎች አተረጓጎም ደንቦች መሠረት እንደ ቤዝ ሜታል ዕቃዎች ሆነው የሚቆጠሩ ከድብልቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ ዕቃዎች ጭምር/ ከያንዳንዳቸው ሌሎች ሜታሎች መካከለ በክብደት ብልጫ ካለው ቤዝ ሜታል የተሠራ ዕቃ እንደሆነ ተወሰዶ ይመደባል፡፡ለዚህ ሲባል፡-

/ሀ/ ብረትና የአረብ ብረት፤ ወይም ልዩልዩ ዓይነት ብረቶች ወይም የዐረብ ብረቶች፤እንደ አንድና አንድ ዓይነት ሜታል ይቆጠራል፤

/ለ/ በመግለጫ 5 በተወሰነው መሠረት፤ አንድ አሎይ እንደ አሎይነቱ የሚመደብበትን አንድ አይነት ሜታል ብቻ ሙሉበሙሉ እንደያዘ ተቆጥሮ ይመደባል፤ እና

/ሐ/ በአንቀጽ 81.13 የሚመደበው ሰርሜት እንደ አንድ ነጠላ ቤዝ ሜታል ይቆጠራል፡፡

